# FORUM FOR SOCIAL STUDIES

## POVERTY DIALOGUE FORUM

*Consultation Papers on Poverty No. 5*




# የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ እና ድህነት ቅነሳ
# The Private Sector and Poverty Reduction

*Edited by*
*Meheret Ayenew*

**Addis Ababa**
**November 2001**

# FORUM FOR SOCIAL STUDIES

## POVERTY DIALOGUE FORUM

*Consultation Papers on Poverty No. 5*

# የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ እና ድህነት ቅነሳ
# The Private Sector and Poverty Reduction

*Edited by*
*Meheret Ayenew*

**Addis Ababa**
**November 2001**

**The opinions expressed in this publication are those of the authors and do not necessarily reflect the views of FSS or its Board of Advisors.**

# ማ ው ጫ

**መግቢያ……………………………………………………………………………. 1**
*ምህረት አየነው*
*የፕሮግራሙ አቀነባባሪ*

**Summary of Presentations……………………………………………………….. 2**

**አምራች ኢንዱስትሪውና ድህነት ቅነሳ………………………………………………… 4**
*ተሾመ ከበደ*
*የጀኒዩን ቆዳ ኩባንያ ዋና ሥራ አስኪያጅ*

**አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች፣**
**መደበኛ ያልሆነ የኢኮኖሚ ዘርፍና ድህነት ቅነሳ……………………………………… 7**
*ሙሉ ሰለሞን*
*የአልሜታ ኢምፔክስ ኃ.የተ.የግል ኩባንያ ም/ሥራ አስኪያጅ*

**የግሉ ንግድ ዘርፍ ሚና...…………………………………………………………. 13**
*ኃይለመስቀል አበበ*
*የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት ምክትል ዋና ጸሀፊ*

**አጠቃላይ ውይይት...……………………………………………………………... 20**

# መ ግ ቢ ያ

በዛሬው ምሽት በምናደርገው ውይይት ጥሪያችንን አክብራችሁ በመገኘታችሁ በማኅበራዊ ጥናት መድረክ ስም ማመስገን እወዳለሁ። የዛሬው የውይይት ርዕስ የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚና ድህነት ቅነሳ የሚል ነው። ማ.ጥ.መ. በሀገራችን ተንሰራፍቶ የሚታየውን ድህነት ለመቀነስ ምን መደረግ ስላለበት የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን የሚያሳትፍ ውይይት በተከታታይ ሲያካሂድ ዛሬ አምስተኛው ነው።

እስከአሁን ባደረግናቸው ተከታታይ ውይይቶች የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ስለድህነት መጠንና ምንነት ያላቸውን ግንዛቤና ችግሩን ለመቅረፍ ምን መደረግ እንዳለበት ወይንም ምን እርምጃዎች እየተወሰዱ እንደሆነ ያገኙትን ተሞክሮ አካፍለውናል።

በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን በገጠርና በከተማ ያለው የድህነት መጠንና ስፋት በጣም አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል። ይኸን ችግር ለመቅረፍ የሁሉንም ርብርቦሽ የሚጠይቅ ሲሆን በተለይም የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ የሥራ ዕድል በመፍጠርና መዋለ ንዋይ በማስፋፋት ድህነትን በመዋጋት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብዬ አምናለሁ።

ስለሆነም በዛሬው ውይይታችን የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ በድህነት ቅነሳው ስለሚጫወተው ሚናና በተለይም ምን ዓይነት የፖሊሲና የአሠራር ሁኔታዎች ቢመቻቹ ነው የበለጠ አስተዋጽኦ ሊያደርግ የሚችለው? በሚል ዙሪያ ጠቃሚ ውይይት እንደምናደርግ ተስፋ አደርጋለሁ።

የእነዚህን ውይይቶች ውጤቶችና ዋና ዋና ሀሳቦች እያሳተምን ለሚመለከታቸው ሁሉ ማለትም ለመንግሥት ፖሊሲ አውጪዎች፣ ዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶችና መንግሥታት፣ መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች፣ ለሙያ ማኅበራትና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ ስናሰራጭ ቆይተናል። በተጨማሪም በድህነት ቅነሳ ላይ የምናደርጋቸውን ውይይቶች በኤፍ.ኤም. ሬዲዮ በሳምንት ሶስት ቀን እናሰራጫለን።

ምህረት አየነው
አዘጋጅ

# Summary of Presentations

[The workshop, which was conducted in Amharic, was chaired by Dr. Zewdie Shibire, Dean of the **Faculty of Business and Economics,** Addis Ababa University].

Ato Teshome Kebede, General Manager of the **Genuine Leather Company**, contributed a paper on "Value Creation and Poverty Reduction". Unfortunately, he was unable to attend in person because of illness and his paper was presented on his behalf by Ato Berhane Mewa, President of **Addis Ababa Chamber of Commerce**. The second paper, on "Smallscale Enterprise, the Informal Sector and Poverty Reduction" was delivered by Wzo. Mullu Solomon, Deputy Manager of **Almeta Impex Company**. Ato Hailemeskel Abebe, Deputy General Secretary of **Addis Ababa Chamber of Commerce**, presented the third paper on "The Private Sector and Poverty Reduction".

Ato Teshome's paper emphasized that poverty reduction can only be achieved through the creation of more value (or wealth) and more employment. This, the paper argued, calls for increased production of goods and services, and greater efficiency of production. Only if the means of production are privately owned will it be possible to forge an efficient economy and improve productivity. It will be the private sector and private sector investment, the paper emphasized, which will play a critical role in economic development. Since poverty reduction is dependent on the creation of more value and more productive assets, it will be Industry, as opposed to Agriculture, that will have a greater role in achieving both objectives. The paper was optimistic that poverty can be reduced and eventually eliminated if there is a sound economic policy that encourages productivity and growth. The paper was critical of ADLI, the government's policy of rural-centered development, which, it argued, cannot serve as an effective strategy for poverty reduction. Among the reasons put forth were: a) agricultural production is based on millions of peasant cultivators whose farm plots are too small to sustain increased surplus production or increased productivity; b) there is increasing fragmentation of land and increasing loss of soil through erosion; c) Ethiopian smallholders are in no position to adopt advanced technology. The author was disappointed that the country does not have a viable national industrial policy. At the very least, his paper argued, such a policy should give Industry as much weight as Agriculture.

Wzo. Mullu, who spoke next, briefly reviewed the poverty situation in the country. Ethiopia, she said, was the poorest country in the world whatever criteria were employed to measure poverty. The effort to reduce poverty was thus a worthy endeavor in which the government and the private sector should form a partnership. Poverty reduction however was a process and not an end; it involves continual change and improvements. Wzo. Mullu argued that small-scale enterprises and the informal sector are neglected but important components of the larger economy. They have considerable potential both in terms of economic growth and employment generation. Even under the difficult conditions existing at present, small-scale enterprises and the informal sector provide employment and livelihood opportunities to a large number of people in rural and urban areas of the country. The speaker noted that the country's industrial and business establishment is dominated by small to medium enterprises and that large-scale enterprises are few in number and less significant in terms of employment and as sources of income. With greater encouragement and a nurturing policy environment, small enterprises and the informal sector can play an important role in poverty reduction. Support to the two sectors in the form of training, financial and credit services, appropriate technology, and land could help improve their chances for growth and greater job creation. She pointed out that large numbers of women engage in these sectors however the women are particularly disadvantaged due to gender bias.

Wzo Mullu made a number of critical comments on the government's *Interim Poverty Reduction Strategy Paper* (IPRSP). First, she said, the document does not clearly show a willingness to involve the private sector in the poverty reduction program. Second, she was critical of ADLI on the grounds that it does not give sufficient importance to the industrial and urban sector of the economy but focuses primarily on agriculture and the rural sector. Productivity improvement, she pointed out, is sought solely in terms of land productivity. ADLI says very little about the important role the private sector can play in economic development. Thirdly, the issue of land tenure was not clearly dealt with, and it was her opinion that a sound land policy has considerable contribution to make to

economic growth and poverty reduction. Wzo. Mullu concluded her presentation by stressing that government and the private sector should be partners in development and should support each other in the common endeavor to reduce poverty.

The third speaker was Ato Hailemeskel from Addis Ababa Chamber of Commerce. He started out by making two important points. One was that poverty reduction will be achieved only through economic growth, and the other that the private sector will have to play a central role if sustained economic growth is to be achieved. It was his opinion that the government's economy development policy fails to give the private sector the importance it deserves. He then went on to discuss briefly the nature of poverty in Ethiopia. He characterized poverty as the lack of basic necessities and of a minimum income. The causes of poverty he believed were unemployment, population pressure, low productivity, and lack of skills. Poverty reduction can be achieved by reducing the number of unemployed and improving income earning opportunities. For the private sector to play an important role in poverty reduction, the following conditions were, he said, essential: freedom of movement; secure conditions of investment; ownership rights and rights of commerce; a competitive and free market environment; and economic activity based on profit-making. More investment from the private sector means more jobs and more revenue for the government. The former thus can play the lead role in employment creation while the latter will be responsible for providing essential services such as education and health.

Ato Hailemeskel then turned his attention to the government's IPRSP, which he found deficient in several respects. It was his opinion that a rural-centered development policy will not succeed in reducing rural poverty much less urban poverty. He believed ADLI has a lot of weaknesses, one of which was that it relegates the industrial sector to a subordinate status. Smallholder agriculture cannot be the engine of growth because it is based on tiny farm plots and productivity is, at best, not growing at the rate required to boost improvements in the broader economy. Even if successes in improving production are achieved, the sector is constrained by the limitations of the local market which is the only market accessible to peasant agriculture. The second deficiency of the IPRSP, which he discussed in some detail, had to do with the issue of trade liberalization and globalization regarding which the Paper should have made a clear statement. Ato Hailemeskel's argument was that since local industry was underdeveloped and employed backward technology, it cannot compete with global industry. Hence, there should be a transition period until the competitive ability of local industry becomes adequate. This, he said, means that the government has to take measures to protect local industry through the transition period. The speaker concluded his presentation by insisting that the private sector should have a role in all aspects of the poverty reduction program including monitoring and evaluation. He informed his listeners that Addis Ababa Chamber of Commerce is planning an extensive program of PRSP participation by the business community.

The main points emphasized by all three papers were the following:

i) no program of poverty reduction will succeed without the active involvement of the private sector, but this has not been given recognition in the government's *Interim Poverty Reduction Strategy Paper* (IPRSP);
ii) poverty reduction can only be achieved through sustained economic growth and job creation, both of which require greater private sector investment;
iii) employment creation as a poverty reduction measure has not been given serious attention in the IPRSP;
iv) for the private sector to play a constructive role there must be an enabling policy environment which should, in particular, promote the rule of law, put in place an efficient administration, do away with corruption in public service, and increase investment in basic infrastructure;
v) ADLI, which gives priority to the rural sector, and which assigns the industrial sector only a minor role, is misguided and will not attain its stated objectives.

All three speakers underlined the importance of broad-based consultation with the private sector on matters having to do with economic development and policy but such consultation, they said, has not being encouraged by the government to date.

What follows is the full text of the papers in Amharic.

# †NWv †é¿«è^rV'å~ –x}r i}]

**ተሾመ ከበደ**
**የጂኒዩን ቆዳ ኩባንያ ዋና ሥራ አስኪያጅ**

*–x}r ŠpE¦¤ †i»Áv*

*–x}r †¿– –¨}r }"?* –x}r ˆ¿ª£†µU £˜–µr ªT± £pE¦£ }'å:: I†¿«è †µY –y £MmE'å ŠEÎF'å †µY ynqN ¶Y £M¨p~}^Ir Aå}ïq ¨q¦G:: I † ¿ – †µY 'å^¼N IéD¿ £–x}r¿ †^ŠÖ µÎq M'i~ ^E–x}r rŒŒEƒ rYµåN EL^ºr £MuE'å –x}r¿ £dL\'å nu }'å:: ^EšéC £–x}r i}] ^rWp± IMLEŠp'å †µY }mW" Aå}ïq LPTr £pš¶¯ LD¿ ¨µm"G::

(IšéC Y˜^ F¨ ˆ¿–~µY Šp¶IœŠå I|F I†«é^ †Im 'å^¼ pš"'åX I}ï ·Nr –y £NFt'å¿ \v IM}¶µY –x}r¿ ˆ¿¬r ˆ¿ªMpTµåLår EM'i OŒX }IY:: EAåEåN ¦dTnŠåFt'å ¼¦h "–x}r MEr N¿ MEr }"?" £MG }IY:: ¼fst mEåIr Aå}ïq p^× ILeT¼ £\ºå„ LG^ Šµå«¤ ¶Y Id¼q ¦Gp¦¦š IéD¿N Š†n›ƒ'å £p\º„ L·EÁ d¼pƒ~ –y ¦GD} \'å ˆ¿ªM¦ªYµ'å IÙG^Ù~ ¦GTdd }IY::)

¦µ,Aå"t'å LG_v ˆ¿ªMŠpEår }IU:: £LG^ \Àt ^Ov ˆ}Y\å £}µU„ ~t'å

±W: *–x}r MEr 'åEø EMªY ˆ¿Šå"¿ N·n pL·o EL Y †ELuG MEr }'å::*

š'å«ép: *–x}r MEr Šd¿ HUY '¨N ŠEÎEér eY L ºµé¦ £EÎE'å MEr }'å::*

Šå¿rb: *–x}r MEr Iééq LN Ô'åI忿 £Mºnd'å Ibq'å Šp''å '¨N Iéµ–E'å MEr }'å::*

]p~'å: *–x MEr L¿µ– £rWÖŒ LnWr ÞEé^ LŠé~ Iåi IîpŒY^p¦¿ d„ ·W ßF Úi Iå"¿Iå" 'åy I… MŒI… †îv †¨ ßí †î¨–^ }'åY NIºéY 'šp Ùt £M¨Iºår MEr }'å::*

]¶: *–x MEr eY –Vs µWm Ø^qG Mš¶± b¿r Iîr 'åa……….*

N~Gmr ˆ}šéAå ¼¦hv IEÎF †µY EM U –Dv IédYIå Š}šéC £pE¤ LG_v M·,r ˆ¿ªMuG †¦º¦¨iN::

LG_t £M¦LEŒpr I†µWv¿ F¨ p¿PWÛs £Mµ,'å –x}r E†µY: E'µ¿: Eª¿n: ERY—r: EmJG: E'·: EqVŒ: EB¨M r: EÞEp‹……. oq £EÎE'å MxIT\n ˆ£pÔºT LD}å¿ }'å:: ˆ}šéC ª·O £\'å G³ MxIW" J¨'r –Y~ M· (social fabrics) ILD~t'å ŠšéC £IEº £AåFv¿N Ã¿dr~ rŠåTr Eé Y †¨vGN::

I†µWv¿ ^FE'å −x}r L d}^ £M¦}]] ¿ ¦En¿ v·Y †]]Ié}r ˆ¿± £EîF £_^pƒ 'µ¿ Á~ EéD¿ ˆ¿ªM¨vG~ I_^pƒ 'µ¿ £pš¶¯ ÚYLåFN £MÔEµ'å¿ ·n Eé¦^µ„ ˆ¿ªM¨vGN ·GÎ }'å::

£−x}r i}]'å ^rWp±~ œ·³r — FMN −x}r¿ L d}^~ nEøN M^'µ− nu EéD¿ ¨µm"G::

## −x}r¿ ELd}^ rŠåTr Eé\»t'å £Mµm µå«©v

−x}r¿ ELd}^ IN~ªYµ'å ¼Tr 'å^¼ £\'å¿ G³ £pÔ¼Z mJY¨ ˆ¿ª"}ƒ LQV¦ ŠLºdN £paE †MWÃ £EN::\'å IpÔ¼Z'å IpE¨N −y'å JnTp\n £W\å £D} ynr mEIîr ELD} ŠÙpƒ ÙF¸r ^FE'å EšéC ÙF¸p LMFr Aå}ïqv¿ IMLutr Š−x}r ˆ¿«é'» EM −T· W\å —¨}pƒ LQV¦ }'å::

\'å AåEå RW PYs µIé EM·,r I'åºîpN ELq'i 'å^»" Ù¸r †E'å:: EšéCN ÙF¸p (personal ego) £pLut ^Gr IL¿ªÙ IpPMWIr RW F¨ 'åºîqM}p¿ EM¸GIr †Lt }"::

£−x}r LPTp £ynr M}^ }'å:: If ynr ‹E £−x}r¿ †^ŠÖ µÎqv AåEå EM^'µ− ¨uFG:: †¿− †µY ¦E'å¿ ynr EJœn IMŠ×ÔG −x}r¿ Ld}^ †¨uGN~ −x}r i}] ^¿G rŠåTqv¿ p¾MV ynr IMÙWr MErN INYr F¨ M}»ºWv¿ ˆ¿ªD} ·GÎ }'å::

ŠšéC −N«M IL}]r −x}r¿ EM^'µ− INYr RW F¨ LPMWr~ NYr¿ L¿ŠmŠn ']„ ¨D~G::

ynr £MÙWr †MWÄv (alternative means of production) "ºîqM £MD}år ª·O IMNTu LQV¦v mE¨ q ngr (efficiency of the ownership of means of production) LD}åN £Mq'i µå«¨ }'å::

£MNTu LQV¦v ¨ q I_^r mEIîr} r EéD¿ ¨vFG::

- IMxIWr
- IL¿·Rr '¨N
- I·G ¨ q RY
- ynr ILPTp Lº}å £p'\}~ †Ff }µY ILD}å Š}šéC _^r †MWÄv 'å^¼ Aå}ƒ'å¿ LNT¼ EéqEÙ £M¨uG µå«¨ }'å::

¦E¿Ir µéšî £MNTu LQV¦v I·G ¨ q ^Y ^ELD~t'å £M¦º¦¨i 'ir ILD}å IšéC Tµ− £p'\}å }¼ov¿ M¿Qr nu ¨IgG::

- Š\'å G³ £pÔ¼Z mJY¨ ¶Y £p»»L LD}å
- E¿nTp ÙX¦M}r~ †¦¦œ ¼¿gh ^EM¦ªY·
- I†}^pƒ L"˜E ¿"¨ Špƒ £RW ˜−G~ 'åºîr Eé¦^µ„ LuEå
- †NWv ˆ¿«è\rV'å~ −x}r i}]
- I†µWv¿ £−x}r i}] ¼Tr 'å^¼ †NWv ˆ¿«è^rV'å ·¿mY dªN M~ EéÁ'r ¨µIG/¨vFG:: EšéC LPTq" NŠ¿¦st
- †µVp ‹Emr £Š× £‹ÛqG v·Y †Šå"¦ †NWv †é¿«è^rV'å I†} ^pƒ †é¿ß^rL¿r n›r ¦E'å £RW ˜−G ELÙºY LuEå
- ˆ¿i^g\î'å p¾MV ˆ\îr IMÙWr (engaged in value creation) ¦E'å¿ £ynr Lº¿ IM]ª·(increasing the stock of national wealth) F¨ £pLPTp LD}å
- p¾MV ˆ\îr IMÙWr F¨ ILPMWpN šFf}p I'åºîr F¨ £pLPTp }'å~ †^pMM„}p (sustainability ensured by the stock of additional wealth created)

EšéC ']„ ŒÙE †é M I†µVp £−x}r i}] ¼Tr 'å^¼ pµIé †^p"Î‰'å¿ ˆ¿«é£ITŒr rŠåTr ]¨\º'å ¦EÔ ^rWp± Š†µVp p¾mÃ Aå}ïqv ¶Y ¦Gpµ~šI nu ]¨D¿ EîF'å —EN £pŠpE'å¿ £˜−µr †i»Á I†·mIå ¦^p"E }'å EMEr ¦^t·WG::

£†ér©É¦ †NWv ˆ¿«è\rV l−x}r i}]'å ,Z·WN 'å\¼ L pŠé¦ £EîE'å¿ −Ya'å¿ ˆ¿«é'» lL¯LV¦ ªT± lé¦¿^ l·¿mY dªN £−x}r M^'µ± LQV¦}r ŠpdL º'å Š^Ya'å ŒÙE †é M ˆŠåG rŠåTr Eé\º'å ¨µmG::

£ˆYa'å ŒÙE †é M 'åºîr Šˆ¿«è^rV'å ŒÙG ¶Y £p¦¦š ‹ED} †^p]\mv¿ †Aå¿N ˆ¿ª'rZ'å ·nY~'å ¼X ˜g ˆ¦LTp ¨d¼G ŠMG †^p]\n £L}¾ '¨N †µVp l¼X ˜g †NWv}r ˆ^‹Aå¿ £ªT\mr¿ v·Y ‹EMºî¿ '¨¿N —EN ˆ³· lpdWTl'å~ lp¦¦šlr £†é M ·¿,}p £MÔGµ'å ¦EdEr £Ù´q ˜g ˆ¿± ¼X ˜g †ELD}å¿ ‹ELµ¿šn £ML» lLD}å L^p‹ŠG ¦Elr µå«¨ }'å::

ŒÙE †é¿«è^rV'å l−x}r i}]'å 'å^¼ pµlé M~'å¿ ˆ¿«¨'» d¨ª'å £¦šår¿ v·Zv ^rWp±'å l†·mlå LYNZ LÙrB EéÔG·Ft'å ¨µmG::

LPTq" v·Zt¿ lAåEr F¨ ŠÙEø L LGŠr ¨uFG

1. ‹EÔ'å ^Y—r £dºEå v·Zt

- £‹ÛqG 'å^¿}r
- £µl¦ ª‹M}r
- mE†é¿«è^rV'å ŠM¦µm'å µå«¨ LµEEå
- ¨CN †œMM¦ pºW»V ¦ªTµ'å LD}å

2. †«é_t v·Zt

- £LPTq" £GMr †'åqY v·Zv (Working Conditions)
- ŒÙE †é M'å £MLWlr N¿N — ¨}r HµY †dÙ W˜¨ †EL Y (absence of a national policy for industrial development)
- £M¦^pMN¿~ d»¨}r ¦E'å £RW L¿Ô^ †EL Y (absence of a reliable and sustainable working environment)

- £J¸v £ª¿ov~ £LLV¦v †'»¼ ·nq" LD¿~ ˆY^lY^ mEL»»N £MÔ¼Ur £RW ˆ}i×r Ln›r (incongruent nature of the regulatory framework and their lack of farsightedness)
- †^p«ªW" v·Zv
- MEf¦ £EîE'å léZŒW\é~ ŠY\åN ¶Y £p¦¦š'å Lå\~
- ngr £EîFt'å mERG» v lM¨L¼}år ^ÙW F¨ LdL¼
- J· †¿− '¼ rYµåN M»p~ 'µ~"}r Ln›p
- £J· £lF¨}r †EL^Ô¿ (incompetence and inefficiency of the judiciary)
- £−¶Ù M»r v·Zv
- ŒÙE †é M" l×¨~¿^ l\'å y¨G~ lpŒ}‹" †ªT±¯p EL º~ŠY lM¦ªYµ'å ¼Tr †µW" ÙXN'YŒ (framework) M»p
- lp~ºG £MªTµå ¼Tsv¿ EM^pmlY †ELOŠY/†ELuG/†EM\n
- l—EN †dÕ £µl¦ ¨šr EL'«ªY £M¦^vEå Aå}ïqv †EL Y

## £−x}r i}]'å ^rWp±

−x}r¿ ELd}^ ¦}»ºT'å lˆYa'å F¨ }'å:: lšé¦N léD¿ †¦Eî v·Zv¿ †GpLEŠpN:: †Aå¿ ¦E'å £LXr ¨q Ll»º^ ŠJœlå n›r ¶Y ˆ£Š× £MB− LD}å¿ £†µVp EN}r Ld}\å¿ £NYr šY £MNTu LQV¦~ ^GpNYr |FdY}r †^ÔFµét¿ ·n†sv EMiTn~

# አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች፣ መደበኛ ያልሆነ የኢኮኖሚ ዘርፍና ድህነት ቅነሳ

ሙሉ ሰሎሞን
የአልሜታ ኢምፔክስ ኃ. የተ. የግል ኩባንያ ም/ሥራ አስኪያጅ

*ድህነትን ለመቅረፍ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ሚና*

ድህነት ምንድነው? ሌሎች የሰጡትን ትርጉምና የድህነት መግለጫዎች ትንተና ውስጥ አልገባም:: የአገራችንን ሁኔታ ሳየው ድህነት የተወሰኑ ዜጐች አንዲት ዳቦ ወይም ቁራሽ እንጀራ ማጣት ብቻ ሆኖ አላገኘሁትም:: አገራችን ከዚህ ጋር ተያይዞ የጽናትም የተስፋም የቁርጠኝነት እጦት፣ ረሃብ ቸነፈር ነው እየገረፋት ያለጠው:: እናም ነገን ቀርቶ ዛሬን ማየት እያቃተን ነው::

እጅ እና እግሩ አእምሮው መሥራትና መፍጠር የሚችል ዜጋ እንዳይሰራ፣ ተተብትቦ በቁም እስር እንዲንገላታ ተደርጓል:: የዚህ ክስተት ውጤት ኢትዩጵያ በአለም አንደኛ ድህ እንድትሆን አድርጓታል::

ሁሉንም ማጣት፣ ክብርንም፣ ኩራትንም፣ ፈጠራንም፣ ሥራ ወዳድነትን፣ ቆራጥነትንም ከሁሉም በላይ ተስፋንም፣ ሰብእናንም ማጣት እንዲደርስባት በመደረጉ ነው::

ይህ ችግር ሁሉም የራሱን ሚና ቢጫወት ሊቀረፍና ብሎም ከጊዜ በኋላ ሊወገድ የሚችል ነው:: ለዚህም የማን ሚና ምንድነው የሚለውን በአጭሩ በሚቀጥሉት ገጾች ውስጥ እገልፃለሁ::

*በአለም አቀፍ ደረጃ ድህነት በምን ይለካል? መግለጫዎቹስ ምንድናቸው?*

የአንድ ሰው ገቢ በቀን ከሁለት የአሜሪካን ዶላር በታች ሲሆን፣ በከተማ አከታተም፣ በገቢ ደረጃ፣ በአማካይ ገቢ፣ በሥነ ሕዝብ ቁጥር፣ ሕዝቧን በመመገብ፣ በምግብ ምርታማነት፣ በሕፃናት ምግብ እጥረትና በሞት ብዛት፣ በመሃይምነት፣ ንፁህ ውሃ በማጣትና በንፅሕና ጉድለት ዜጎቿን በማሳደግና በእውቀት በሙያ በማጎልበት ወ.ዘ.ተ በሁሉም ቢታይ በደረቀ ቁጥር ለማዘን ካልሆነ በስተቀር ሁኔታውን አይለውጠውም:: በሁሉም መልኩ አገራችን ድሃ ናት:: ቁጥርም ሳናይ እንዲሁ ከእለት ተእለት ኑሯችን የምናየው ክስተት በመሆኑ ብዙ ጥናትና ማስረጃ የሚሻ ጉዳይ አይጠደለም::

እንግዲህ አገራችን ከላይ በተገለፁት መስፈርቶች በየትኛውም የተሻለች ሆና አልተገኘችም:: በአብዛኛው ከአለም የመጨረሻ ድሃ ናት::

ከላይ የተገለፀውን የአገራችን የድህነት ሁኔታ ለመቅረፍ ምን መደረግ አለበት? ይህን ለመቅረፍ ተገቢ ምላሽ እንዲሰጥ የሚጠበቅበት ማነው? ለምን? ከመንግሥት፣ ከግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ፣ ከሲቪል ሕብረተሰብ ወ.ዘ.ተ ምን ይጠበቃል? እንዴትስ ማሳተፍ ይቻላል? ምን ከማን ይጠበቃል የሚለውን ለማየት እንሞክራለን::

*የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ሚና*

ቀደም ሲል በነበረው አመለካከት የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ትርፍ ለማጋበስ ብቻ እንደቆመ ይቆጠር ነበር:: ነገር ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ ከብዙ አገሮች ልምድና እድገት እንደታየው የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ለሕብረተሰብ ሰላማዊ አር /Social Wel beingness/ ለአካባቢ ደህንነት /Environmental Issues/ ደንታ ሳይኖረው ለትርፍ ብቻ እንደሚንቀሳቀስ መታየቱ ስህተት መሆኑ ተረጋግጧል::

በእርግጥ በአንዳንድ መንግሥት በሚሳተፍባቸው ጉዳዩች ላይ የግሉ ነጋዴ ሊገባ አይችልም:: ለምሳሌ እንደ አገር መከላከል፣ ከዚህም ሌላ ውሃ፣ ትምህርት ጤና ወ.ዘ.ተ ለመንግሥት ተከልሎ የነበረ እንደ ቋሚ ልማድ የሚታይ ጉዳይ ነበር::

ለአገር እድገት ግለሰቦች፣ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ በተቋም መልኩ፣ ሲቪሉ ሕብረተሰብ በጥቅሉ እንደማይሳተፉ አድርጐ መመልከት በተግባር ሲታይ ስህተት እየሆነ መጥቷል:: መንግሥትና የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች እንደ ሁለት ተፃራሪ አለማ እንዳለው አካል ሳይሆን ተደጋጋፊ እንደሆኑ ተረጋግጧል:: ብዙ ልምዶችም ተገኝተዋል::

መንግሥት የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ፣ ግለሰቦችንና የሲቪል ሕብረተሰቡን የነዚህን አላማና ክንውን በሚያቀናጅ መልኩ የሚያሳትፍ መሆኑ ቀርቶ እንደ አንድ ተገንጥሎ የሚገኝ ፍፁም አካል ይታይ የነበረው ጽንሰ ሃሳብ እየቀየረ በመምጣቱ፣ መንግሥት ያለ ሕብረተሰብ ምንም ማለት እንዳልሆነ ተረጋገጧል::

የተለያዩ አገሮችንም እድገትና ልምድ ስናይ ያለው ልዩነት እጅና ጓንት ሆኖ የመሥራቱን አጋጣሚ የመጠቀምና ያለመጠቀም ልዩነት ነው የሚታየው:: እጅና ጓንት ሆነው የሰሩ አገሮች ውጤታማ እየሆኑ ነው:: ይህን ለማድረግ የሚጠራጠ

ሩ ደግሞ ውጤታቸው በእድገትም ሆነ በልማት ባለበት የመርገጥ ወይም ወደ ኋላ የመመለስ አዝማሚያ እንዳሳዩ በርካታ ተጨባጭ መረጃዎች ያመለክታሉ።

እጅና ጓንት በመሆን ሰርተው አገራቸውን ከድህነት ካወጡ አገሮች በጥቂቱ ብንጠቅስ፣ ለምሳሌ የደቡብ እና የደቡብ ምሥራቅ አገሮች፣ ቻይና፣ ማሌዢያ፣ ታይዋን በቅርቡም ቬትናም ፣ ሕንድ፣ ከአፍሪካም ቦትስዋና ሞሪሽየስ ድህነትን ቀርፈው ከፍተኛና አስደናቂ ለውጥ ለማምጣት በቅተዋል። ይህ ውጤት ደግሞ በኢኮኖሚ ዘርፍ ከፍተኛ ሚና ከሚጫወተው ከግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ውጭ የተገኘ ውጤት አይደለም።

ስለዚህ ድህነትን የመሰለ መዋቅራዊ /Structural/ ችግር መፈታት ካለበት የግዴታ መንግሥትና የግሉ እንዲሁም የሲቪል ሕብረተሰቡ እጅና ጓንት ሆነው የመንቀሳቀስ ጉዳይ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው።

የኢትዩጵያ ኢኮኖሚ ምንግዜም ኋላ ቀር እና ከእጅ ውደ አፍ ከመሆን ያላለፈ ሲሆን እስከ ዛሬ ባለው ልዩ ልዩ ተከታታይ አስከፊ የጦርነት፣ የድርቅ፣ በአጠቃላይም ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ችግሮችን /ቀውሶችን/ ተቋቁሞ ሕዝቡ አሁን ወዳለበት ዘመን እንደ ሕዝብ ለመድረስ ችሏል። ይህም ሁኔታ የሚያሳየኝ ሁሉም የራሱን ድርሻ ሊወጣ የሚችልበት ሁኔታ ቢመቻች ድህነትን ሊቀርፍ ከጊዜ በኋላም ሊያስወግድ የመቻሉ እድል ሰፊ እንደሆነ ነው።

በእርግጥ ድህነት በቁሳዊ እርካታ ብቻ የተሟላ ምላሽ ሊያገኝ የሚችል ክስተት አይደለም። ይልቁንም ማሕበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሰብአዊ ፍላጎቶች በተመጣጠነ መልኩ ሊረኩበት የሚያስችል አጠቃላይ ማሕበራዊ ለውጥን የሚጠይቅ ነው።

ስለዚህ ድህነትን የመቅረፍም ይሁን የማስወገድ ጥረትን የምመለከተው እንደ ሂደት እንጂ እንደ ግብ አይደለለም። ሂደትን የምንቀበል ከሆነ፣ ለለውጥ የተዘጋጀን መሆን አለብን። በአንድ ወቅት የሚደረግ ጥረት ብቻ ተደርጎ መወሰድ የለበትም። ቀጣይነት ያለው ጥረት ደግሞ ማሕበራዊ፣ ግለሰባዊ፣ ተቋማዊ ይዘት የሚያካትት መሆን አለበት።

ከዚህ አንፃር ወደ ዋናው ርእሴ ልመለስና የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ድህነትን በመቅረፍ ረገድ ሊጫወት የሚችለው ሚና ምን መሆን አለበት?

1. <u>መደበኛ ያልሆነ ክፍለ ኢኮኖሚ /Informal Sector/</u>

መደበኛ ያልሆኑ፣ የኢኮኖሚ ክፍሎች በአገራችን ለመሥራት አመቺ ሁኔታ ሳይፈጠርላቸው እንኳ ድህነትን ለመቅረፍ የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነው።

መሬት፣ ፋይናንስ ወይም ለብድር አገልግሎት ቅርበት የላቸውም። ይህም ሳይኖራቸው፣

- የሚፈጥሩት ሥራ፣
- የሚያቅፉት የሕብረተሰብ ክፍል
- የሚሰጡት ግልጋሎት ቀላል አይደለም።

እንዲያውም ለፍፁም ድህነት መቀነስ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያደረገ ያለው ይኸው ንኡስ ክፍለ ኢኮኖሚ ነው።

2. <u>አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች</u>

በማደግ ላይ ያለው የግሉ ክፍለ አኮኖሚ መደበኛ ያልሆኑ፣ አነስተኛና መካከለኛ እንዲሁም ትልቁን የሚጨምር ሲሆን በአገራችን ትልቅ የሚባሉ የግል ኢንዱስትሪዎችና ኢንተርኘራይዝ አሉ ለማለት አያስደፍርም ያሉትም መካከለኛ ሲሆኑ እነሱም በጨርቃ ጨርቅና በመጠጥ ኢንዱስትሪ ወ.ዘ.ተ ያሉ ናቸው።

በየትኛውም ያደጉ አገሮች ልምድ ስናይ ትልቅ ሆነው የጀመሩ የሉም። መደበኛ ሆነው አነስተኛና መካከለኛ የነበሩት እያደጉ ወደ ትልቅ ኢንዱስትሪ በማደግ፣ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ለአንድ አገር ድህነትን ለመቅረፍና ለማደግ የማእዘን ድንጋይ መሆናቸውን አስመስክረዋል።

በአገራችን ግን፣ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ቀደም ብሎ በነበረው አመቺ ያልሆነ ሁኔታ ሲወገዝ የነበረ ክፍል ነው።

- ላለፉት 30 ዓመታት በፖሊሲ ሰረገጥ፣
- ከዚያ በፊት ደግሞ በባህልና በአመለካከት ሲገለል የነበረ ክፍል ነው።
- አሁን ደግሞ ገና ሲፍጨረጨር በራስ የመተማመን ስሜቱን ይበልጥ ማጐልበት በሚችልበት ሁኔታ ላይ አይገኝም።

ይህ ክፍለ ኢኮኖሚ፣ ምንም አመቺ ሁኔታ ሳይፈጠርለት፣ መጉላላት፣ እየደረሰበትም በመሥራት፣ ድህነትን ለመቅረፍ በሚጫወተው ሚና ከመንግሥት የተሻለ ድርሻ እንዳለው በግልጽ ያሳያል።

አሁን እንኳ ከአጠቃላይ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ፣ መደበኛ ያልሆነው ትልቅ ድርሻ አለው። ስለዚህም እራሱ የሚያድግበትን ሁኔታ ማመቻቸት ያስጠ

ፈልጋል:: ለምሳሌ፣ ድህነትን ለመቅረፍ ከሚያደርገው አስተዋፅኦ አንዱ የባንኮች የቁጠባ ሂሣብ ሲታይ መደበኛ ያልሆነ ክፍል እስከ ብር 10,000.00 የሚያስቀምጠው 90 ከመቶ የቁጠባ ሂሣብ ይይዛል:: ሆኖም ግን በሚያደርጉት አስተዋፅኦ አንፃር ለብድር እድል የላቸውም:: ከዚህም ሌላ በዚሁ ክፍለ ኢኮኖሚ ከባንክ ውጭ የሚንቀሳቀስ ገንዘብ ቀላል አይደለም::

በዚሁ አንፃር በአዲስ አበባ እንኳን መደበኛ ያልሆነ ሠፈራና የመጠለያ ግንባታ ሲታይ ከፍተኛ የፋይናንስ ምንጭ ከእቁብና መደበኛ ካልሆነ ክፍለ ኢኮኖሚ የተገኘ መሆኑ ተረጋግጧል::

ይህ እራሱ ካላቸው ከፍተኛ የሥራ ፈጠራና ገቢ ማስገኛ ሚና ባሻገር እያበረከተ ያለው ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ አስተዋፅኦ ቀላል አይደለም:: ይህን ሲያደርጉ ደግሞ ለምሳሌ፣ ብድርን ሲ ተገብሩ እንደ ባንኮች ከባድ ዋስትና ባለመጠየቃቸውና ቀለል ያለ የብድር አበዳደርና ልውውጥ ስለሚከውኑ ከኢኮኖሚ ግቦች ግንኙነት አልፎ፣ ለማሕበራዊና ሰብአዊ አላማዎች እንደ ተሳትፉ የሚያሳይ በመሆኑ ሊበረታቱ ይገባል:: ለምሣሌ የአዲስ አበባ አጠቃላይ ምርት ብንመለከት መደበኛ ያልሆኑትን ትተን ግብር ከፋዩን አነስተኛና መካከለኛ የግል ክፍለ ኢኮኖሚ አስተዋጽኦ ብናይ እንደሚከተለው ይሆናል::

የአዲስ አበባ አጠቃላይ ምርት በ1986 ዓ.ም. ብር 6 , 731.5 ሚሊዮን ፣ በ1987 ዓ.ም. ደግሞ ብር 7 , 652.6 ሚሊዮን ሲሆን የአነስተኛ መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች /በታክስ መክፈል የሚታወቁት ብቻ/ የአስተዋጽኦ ድርሻ 1986 ዓ.ም. ብር 2 , 168.7 ሚሊዮን /32.2 %/ በ1987 ዓ.ም. ደግሞ ብር 2 , 990.2 ሚሊዮን /39.4 %/ መሆኑን ተገልጿል:: /የአዲስ አበባ ከተማ 1986 እና 1987 አጠቃላይ ምርት ሪፓርት ያሳያል::/

ከዚህም ሌላ መደበኛ ባልሆነ ክፍለ ኢኮኖሚ የሚሳተፉ ሰዎች ብዛት ትልቅ ግምት የሚሰጠው ነው:: ሥራ በመፍጠር ድህነትን ይዋጋሉ::

ለግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ የተመቻቸ ፖሊሲ ይቀረጽ ስንል፣ ይህ መደበኛ ያልሆነ አካል እየተጫወተ ያለውን ሚና እንዲያጎለብት ብሎም ወደ መደበኛ እድገት እንዲጓዝ ይደረግ ማለታችን ነው::

አሁን እየከወነ ያለውን ድህነትን የመቅረፍ ተግባር በተጠናከረ መልኩ የሚወጣበት ቅድመ ሁኔታዎች ይፈጠሩ ማለታችን ነው::

በሁሉም አገሮች በተለይም በታዳጊ አገሮች አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች፣ ለዜጎች የሥራ እድል በመፍጠር፣ በማሕበራዊና ለኢኮኖሚያዊ እድገቶች ስለሚያደርጉት ከፍተኛ አስተዋፅኦ፣ በአለም አቀፍ ሠራተኞች ድርጅት /ILO/ ለአመታት እውቅና ተሰጥቷል::

የአለም አቀፍ ሠራተኞች ድርጅት የሥራ አመራር ማሳደጊያ መርሃ ግብር፣ እ.ኤ.አ ከ1950ዎቹ ጀምሮ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን ለማስፋት ባደረገው ጥረት፣ የፖሊሲዎች፣ የህጎችና የአፈፃፀም ሁኔታዎች /Policy & Regulatory Environment/ መመቻቸት፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ለሚያመርቱት ምርትና ለሚያቀርቡት ግልጋሎት፣ የገበያን ፍላጎትን ጭምር ያስፋፋል:: ካልተመቻቸ ግን የገበያ ፍላጎትን ይወስናል ተፅእኖም ያደርጋል::

የፈቃድ የምዝገባ አፈፃፀም፣ ቢሮክራሲያዊ፣ አድካሚ፣ ውጣ ውረዳቸው የበዛ፣ ጊዜ የሚፈጁ ከሆኑና፣ ለተጠቃሚው ግልጽ ካልሆኑ፣ ለኢንተርፕሪነሩ፣ የልውውጥ ሸክም ይሆኑበታል:: ከዚህም ሌላ ከመጠን ያለፈ የገበያ ቁጥጥር፣ የመንግሥት ያለአግባብ በየንግዱና በየኢኮኖሚው ክፍሎች ጣልቃ መግባትና እራሱ ነጋዴ መሆን የኢንተርፕሪናል ፍላጎትና ስኬት እንዲዳከም ብሎም እንዲሞት ያደርጋል::

ፖሊሲና የአፈፃፀም ሁኔታዎች ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራዞች የቀጥታ ድጋፍ ሰጪ ፕሮግራሞችንም አስተዋፅኦ ሊወስኑ ይችላሉ ለምሳሌ፣ እንደ ገበያ ድጋፍ ሰጪ ፕሮግራሞችን ሊወስኑ ይችላሉ:: በአነስተኛ ሥራዎች ላይ መንግሥት ጣልቃ ሲገባ፣ ትንሹን ያጠፋል በትልቁ ስለሚገባ ቅልጥፍና የለውም፣ የሥራ ማስኬጃ ወጪ ይበዛል:: ትንሾችን ለጊዜው ያጠፋል ፣ ድርሻውን በበቂ አይወጣም ገበያውን እንደ ትንንሾቹና መደበኛ እንዳልሆኑት እታች ድረስ ወርዶ ለማግኘት አይችልም:: ትንንሽ ንግዶች ውስጥ መንግስት ገብቶ ይሥራ ማለት ውጤታማ ካለመሆኑም አልፎ ያረጀና ያፈጀ አመለካከት ነው:: በአነስተኛ ሥራዎች ላይ የግሉ አስተዋጾ የተሻለና ትርፋማ ገቢ ግለሰቦች እንዲያገኙ ያደርጋል::

መንግስት መግባት ካለበት አገራትን አንፃራዊ ጠቀሜታ በምታገኝባቸውና ትልልቅ በሆኑ መስኮች ከግሉ ጋር በመደጋፍ ቢገባ ውጤቱ ያማረ ይሆናል:: ለአነስተኛና ለመካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እድገት ቀጥታ ድጋፍ የሚሆኑ፣ እንደ ገበያ ድጋፍ፣ የሥራ አመራርና የሙያ ስልጠና ሴሚናሮች፣ ወቅታዊ ቴክኖሎጂዎችን የማሳወቅ፣ ብድርና ፋይናንስ የሚገኝበት ዘዴ ሁሉ፣ በተለይም መሬትና የመሠረተ ልማት አቅርቦት፣ አጠቃላይ የፖሊሲና የአፈፃፀም ሁኔታዎች /Environment/ ካልተመቻቸ አመኢ ለዘለቄታው ስኬታማ ለመሆን ያግዳቸዋል ድህነትን ለመቅረፍ የሚጫወቱትን ሚና ይገድበዋል::

ስለዚህ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን ለማስፋፋት ምርጥ ዘዴ ሆኖ የሚታመነው ለአነስተኛ፣ ለመካከለኛና ለትልቅ ኢንተርፕራይዞች ድጋፍ ሊሰጡ የሚችሉ ፖሊሲዎችን ማውጣትና አፈፃፀማቸውን መከታተል ነው::

## የፖሊሲና የአፈፃፀም ሁኔታ በአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች /አመኢ/ እድገት ላይ

አመኢን ማሳደግ የሚያስፈልግበት አለማ ምንድነው? አመኢን ማስፋፋት የአገርን እድገት ግብ ለመምታት ከሚመረጡት ውጤታማ ዘዴዎች አንዱ ነው:: ይህም በመሆኑ ለሚከተሉት ብሄራዊ ጉዳዩች ይረዳል:: ድህነትን ለመቅረፍ፣ ብሎም ለማስወገድና የሥራ እድል ለመፍጠር፣ የኢንዱስትሪንና የምርትን መሠረት ለማሳደግ፣ የተመጣጠነ እድገት ለማምጣት፣ እናም ብሄራዊ ማሕበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማምጣት::

ስለዚህ አመኢ ለአገር፣ ለማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ለማድረግ፣ በሚንቀሳቀሱበት አካባቢ ባለው ፖሊሲና የአፈፃፀም ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ ይወሰናሉ:: ለምሳሌ ለኢንተርፕርነርስ ጥላቻ ባለበት የቢዝነስ አካባቢ በሚከተሉት ሁኔታዎች ስኬታማ ሆነው ሊሰሩ አይችሉም::

1. ያሉት ፖሊሲዎች ለአመሚ አሉታዊ ተፅእኖ ላላቸው ክፍለ ኢኮኖሚዎች ብቻ የቆሙ ከሆኑና መሬት፣ ፋይናንስ፣ መሣሪያ፣ ጥሬ እቃና ግብአቶች ማግኘትን ከባድና ውድ የሚያደርጉባቸው ከሆነ አድሎአዊ ውድድር እንዲፈፀምባቸው ከተደረገ፣
2. ምዝገባና ፈቃድ፣ አመኢ በተወሰኑ ገበያዎች እንዳይንቀሳቀሱ የሚያግድ ከሆነና ተግባራዊ ሊሆኑ የማይችሉ ገደቦችና የንግድ አፈፃፀሞች ካሉ፣
3. የተወሰኑ ሕብረተሰብ ክፍሎች ወይም ዜጎች፣ ውጤታማና አስተማማኝ በሆኑ ኢንተርፕራይዞች ውስጥ እንዳይሳተፉ በሕግ፣ በባሕል፣ በማሕበራዊ ጉዳዩች የሚታቀቡ ከሆነ፣ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሴቶች በሕግ፣ በባሕል፣ በሃይማኖት ወ.ዘ.ተ ይታቀባሉ::
4. በባለስልጣናት በኩል የጉቦኝነትና የምዝበራ ልምድ ካለ፣

ከላይ የተገለፁት ሁኔታዎች ካሉ ፖሊሲዎችንና አፈፃፀማቸውን መመርመርና ለአመኢ እድገት አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩና የሚያበረታቱ ለውጦች ማምጣት በጣም አስፈላጊ ነው:: በኢኮኖሚው ተዋናዩች፣ በአገር ውስጥና በውጭ ኢንቨስተሮች መካከል እምነት ለመገንባት በገበያ መሠረት የሚመራ ጤናማ የሆነ የኢኮኖሚና የቢዝነስ አካባቢ /Environment/ መኖር፣ ለአመኢ እድገት በጣም አስፈላጊ ነው::

የአመቺ ፖሊሲዎች መኖር ብቻውን ለአመኢ እድገት በቂ አይደለም:: የአመኢ ማስፋፊያ መርሃ ግብሮች ለተበደደሉ፣ ለተጎዱ አካባቢዎችና ማሕብረሰቦች ክፍሎች፣ የተለዩ ሁኔታዎች ማመቻቸት አለባቸው:: ለምሳሌ ለሴቶች ልዩ ልዩ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት የአፍሪካ ሴት ኢንተርፕሪነሮች በጣም ዝቅተኛ መቶኛ ይሸፍናሉ:: ይህም አድሎአዊ ሕጎች፣ የንብረት ባለቤትነት እጦት፣ የትምህርት የስልጠና፣ የጤና የብድርና የመሳሰሉት እጦት ሲሆን በአጠቃላይም በማህበራዊ ሃይማኖታዊ ባህላዊና ወ.ዘ.ተ ተጽእኖዎች መሆኑን እንገነዘባለን:: ስለዚህ፣ የአመኢ ማስፋፊያ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች፣ የአመኢን ዋና ዋና ፍላጎቶች ማሟላት አለባቸው::

መሬት የማግኘት፣ ብድር፣ ስልጠናና ትምህርት የማግኘት፣ በሴቶች ጉዳይ ላይ፣ በኢመኢ ማስፋፊያ ላይ ያተኮሩ ህጎችና ሕግጋቶች፣ ወ.ዘ.ተ፣ ተግባራዊነታቸው መረጋገጥ አለበት:: ለምሳሌ ሴቶች በጾታቸው ምክንያት በሕግ፣ በሃይማኖት፣ በኢኮኖሚ በሕብረተሰባዊ፣ በባህላዊ ሁኔታዎች የሚደርስባቸው ተፅእኖ እንዲወገድ ለማድረግ የተነደፈ ፖሊሲና መርሃ ግብር ካለ፣ አፈፃፀሙን ተግባራዊ ለማድረግ መከታተል ያስጠፈልጋል::

ለሴቶች የታቀደው ድጋፍም ሆነ ማበረታቻ፣ ለነሱ መድረስ አለበት:: አለበለዚያ ስለጉዳዩ በጎ ፍላጎት ማሳየት ብቻውን ሴት ኢንተርፕሬነሮችን ለማፍራትም ሆነ ለማሳደግ አይረዳም::

ቢዝነስ ለመጀመር ሥራው ውስጥ ለመቆየትና ለማካሄድ፣ እንደ የንብረት ባለቤትነት ሕጎች፣ ኮንትራትና ግዴታዎች፣ የሥራና የንግድ ፈቃዶች፣ ኃይልና መገልገያዎችን ለመትከል የሚያስፈልጉ ፈቃዶች፣ታክሶች ወ.ዘ.ተ ኢንተርፕሪነሮችን የሚያበረታቱና የሚተገበሩ መሆን አለባቸው:: ይህም አዲሶች እንዲቋቋሙ ነባሮች እንዲበለፅጉ ለማድረግ ያስችላል::

## የመሸጋገሪያ የድህነት ማቃለያ ስልት ሰነድ (Interim Poverty Reduction Strategy Paper 2000/01 - 2002/03

ቀደም ብለን የድህነት መገለጫዎችና መስፈሪያዎች ለማየት በሞከርነው መሠረት፣ ከመንግሥት፣ ከግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ፣ ከሲቪል ሕብረተሰቡ ምን ይጠበቃል? እንዴት ነው መሳተፍ የሚችሉት? ከዚህ አንፃር በኢትጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት አማካይነት ተዘጋጅቶ ለአለም ባንክ የቀረበውን የመሸጋገሪያ የድህነት ማቃለያ ስልት ሰነድ ይዘቱ ምንድነው? ለተገለፁት የድህነት

መግለጫዎች ምላሽ ለመስጠት በቂና የተሟላ ነው ወይ?

ስልቱ በአጠቃላይ ጥሩ ነው:: ነገር ግን የእድገት የመሠረት ድንጋይ የሆነውን የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ፣ እንዲሁም የሲቪል ሕብረተሰቡን ጭምር እንዴት እንደሚያሳትፍ ቁልጭ አድርጎ ባለማሳየቱ ውጤታማነቱን አጠራጣሪ ያረገዋል::

ሀ. <u>የግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት ስልት /ALDI/</u>

ድህነት መዋቅራዊ ችግር መሆኑ ግልፅ ነው:: የከተማም የገጠርም ክስተት ነው:: በመሆኑም የገጠርና የከተማ ልማት ቅንጅት ያስፈልገዋል ማለት ነው:: የግብርና ኢንዱስትሪላይዜሽን ስንል ከመጀመሪያ ደረጃ ምርት ወደ ሌላ የፋብሪካ ሂደት / Processing / ወደ ሁለተኛ ምርት ገበያ መሸጋገር ማለት ነው::

በአንድ በኩል የግብርና ምርታማነትን መጨመር ማለት በሌላ በኩል በግብርና ላይ አላግባብ የተሰማራውን ተረፈ ጉልበት በሌሎች የምርት መስኮች ማሰማራት ማለት ነው::

ይህን ለማድረግ ደግሞ ግብርናን ኢንዱስትሪላይዝ ማድረግ፣ የገጠሩን አሰፋፈር ወደ ከተማ መለወጥ ነው:: ወደከተማ ለመለወጥ ደግሞ በከተሞች አካባቢ መስፋፋት የሚገባቸውን ግብርና ያልሆኑ ክፍለ ኢኮኖሚዎችን ማስፋፋት ማለት ነው:: ይህ ሊሆን የሚችለው የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ሲበረታታና ኢንተርፕራይዞችን ማቋቋም የሚቻልበት ፖሊሲና ድጋፍ፣ የአፈፃፀም ቀናነት ሲኖር ነው::

በተለይ ኢንዱስትሪ ለማቋቋም ይሁን ለማስፋፋት፣ በገጠርም ይሁን በከተማ የኢንተርፕርነርሽፕ ስሜትና ፍላጎትን ለማሳደግ የመሬት ባለቤትነት፣ የጥሬ እቃዎች በተመጣጠነ ዋጋ መገኘት የቴክኖሎጂ ግኝትና የሰለጠነ የሰው ሃይል ማግኘት ወ.ዘ.ተ ትልቅ አስተዋፅኦ አለው:: ለዚህ ደግሞ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚም መንግሥትም በመጫወት ያለባቸውን ሚና አልተጫወቱም:: ስልቱ ላይም አልታየም የነዚህ ሁኔታዎች መልስ አለማግኘት፣ ግብርና መር ልማት /ግመል/ /ADLI/. ከዚህ አንፃር የቀየሰው ግልጽ የልማት እስትራተጂ አለመኖር፣ መንግሥትንም ሆነ የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ የሚያሳትፍ ግልፅ የሆነ ክፍላተ ኢኮኖሚያዊ ስልት አለመኖር ነው:: እስከሌለ ድረስ መዋቅራዊ መንስኤ ላለው ድህነት ስልቱ ሊሰጥ የሚችለው ምላሽ ብቃቱ አጠራጣሪ ይሆናል::

ለ. <u>የሕግ ተቋማትና የመንግሥት አስተዳደር ማሻሻያ</u>

በዚህ ረገድ መንግሥት የተለያዩ የማሻሻያ ፕሮጀክቶች ፕሮግራሞች እንዳሉት በልዩ ልዩ መገናኛ ብዙሃን ይሰማል:: እነዚህ ሲጠናቀቁ የተቀላጠፈ የፍትህና የመንግሥት አስተዳደር አገልግሎቶች እንደሚኖሩ ተገልጿል::

ይሁንና እምን ደረጃ ድረስ ከመንግሥት ውጭ ላሉት አካላት ማለትም የግል ክፍለ ኢኮኖሚንና ሲቪል ሕብረተሰቡን እንደሚያሳትፍና የነሱንም ሚና እንደሚያጐለብት አያሳያም::

የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ እንዲያድግና ድህነትን ለመቅረፍ ብሎም ለአገር እድገት የበኩሉን ከፍተኛ ሚና ለመጫወት እንዲችል ፣ የራሱን ፍላጐትና አስተያየት ሊያንፀባርቅ በሚችል መልኩ መዘጋጀቱን የሚያረጋግጥ ነገር የለም::

ያልተካተቱት እየታዩ የሚካተቱ ከሆነ መቼ ነው ? ተጀምረው እየተካሄዱ ያሉ ቢሆንም ፣ ለማሻሻል የሚደረግ ቅድመ ዝግጅት የለም ::

ሐ. <u>ኢመአከላዊነትና ለስልጣን ተሣትፎ ማብቃት</u>

በመንግስት መዋቅር ላይ ኢመአከላዊነት አለ:: በክልልና በፌደራል የሚታየውን ያህል በመንግስት አደረጃጀትና በክልል ተዋረድ አይታይም:: ህዝቡ ወደሚገኝበት አካላት አይወርድም:: ሃሣብ በመቀበልም አይሳተፍም::

አዋጆች ከመውጣታቸው በፊት ጉዳዩን በሚተገብሩት አካላት እንደየግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ አካላትና ሌሎች ፣ በቂ ተሳትፎ እንዲያደርጉና ቀድመው እንዲመክሩበት አይደረግም::

የልማት እስትራቴጂ በፌደራልና በክልል ሲታይ በዝግጅት ሂደት ውስጥ ፣ የእድገት ፣ የመዓዘን ድንጋይ የሆነውን የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ይቅርና ፣ በመንግስት መዋቅር እንኳን የወረዳንና የቀበሌን አያሳትፍም:: በአብዛኛውን ጊዜ ከላይ ሲወርድ ይታያል::

መ. የአቅም ግንባታ

ድርጅታዊም ይሁን ግላዊ የአቅም ግንባታ እናከናውናለን ስንል ፍላጎታችን (need) እንዴት ነው ፡ ለይተን የምናስቀምጣቸው:: የዚህ እስትራቴጂ አልተቀመጠም:: የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ከዚህ ተጠቃሚ እንደሚሆን በአጭሩም እንኳ ባለመጠቆሙ አፈፃፀሙን አጠራጣሪ ያደርገዋል:: ከግሉም የሚጠብቀውን አያሳይም::

በመንግሥት የሚሰጡ ትምህርቶች እርዳታ ከሚሰጡ ተዘጋጅተው ከመምጣት በስተቀር ከራሳችን ፍላጎት ተነስቶ አይደለም:: እንዲያውም በይበልጥ ቢሮክራሲያዊ ...... መሆኑ ይታወቃል::

የሰው ሃይል ስልጠናን እና የቴክኖሎጂ እውቀት ማዳበርን አስመልክቶ አገራችን የበለጠ ተፎካካሪ የምትሆንበት መስክ ተጠንቶ፣ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚም ይሁን መንግሥት የየድርሻቸውን ተደጋግፈው ካልተወጡ ስልቱም በረዥም ጊዜ ተከታታይነት እንዲሰራ ካልተደረገ አገር ከድህነት ወጥታ ታድጋለች ማለት "ላም አለኝ በሰማይ ይሆናል" ::

ማጠቃለያ

1. የግሉ ክፍል የፈጠራ ምንጭ መሆኑን መቀበል

2. ግለኝነትንና የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚውን አንድ ዓይነት ጽንሰ ሃሣብ እንደያዙ አድርጎ መመልከቱ ስህተት መሆኑን ማወቅ፣ ግለኝነት በየትኛውም በመንግሥትም በሲቪል ሕብረተሰብ ወ.ዘ.ተ ሊገለጥ የሚችል ባህሪ መሆኑን መገንዘብ::

3. የመሥራት ባህልን ጠቃሚነት በማሳየት ረገድ፣ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ታላቅ የእውቀት ምንጭ መሆኑን በተለያየ መድረክና የብዙሃን መገናኛ መግለፅ፣

4. ይኸው ክፍለ ኢኮኖሚ ድህነትን መቅረፍ እንዲችልና ብሎም ለአገር እድገት ከፍተኛ ሚና እንዲጫወት የሚያስፈልገውን ፖሊሲ መፍጠርና አፈፃፀሙንም መከታተል በአፈፃፀም የሚታዩ ደካማና ጠንካራ ጎኖችን አይቶ በወቅቱ መፍትሄ መሻት፣

5. በድህነት ቅነሳ ስልት አቀራረጽም ሆነ ትግበራ ላይ የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ሚና በግልፅ ማስቀመጥና ማሳተፍ ያስፈልጋል::

6. ይህንኑ ስልት ለማስፈፀም በሚቀየሱ ሌሎች ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ፖሊሲዎች ቀረፃ የግል ክፍለ ኢኮኖሚ ተሳትፎ ደረጃ በደረጃ ማሳደግና የባለቤትነት ስሜት እንዲያድርበት ማድረግ፣

7. በመንግሥትና በግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ መካከል የልማት ሽርክና እንጂ ተፃራሪነት እንደሌለ፣መገንዘብና ሕብረተሰቡም የአመለካከት ለውጥ እንዲያመጣ ጥረት ማድረግ፣

8. በኢኮኖሚና በማሕበራዊ ዘርፎች የሚታዩት ልዩነቶች የድሮ አስተሳሰብ መሆናቸውን እንረዳለን:: ለምሳሌ፣ የከተማ አስተዳደሮች /ማዘጋጃ/ ይሰራ የነበረውን ቆሻሻ ማንሳት፣ መሰብሰብ ወ.ዘ.ተ የግሎቹ ወጪ ሳያበዙ፣ ወረፋ ሳያስጠብቁ በተቀላጠፈ ሁኔታ ፍትሃዊነት ሳያጓድሉ ይሰራሉ:: ከዚህ ለመማርም መዘጋጀት የግድ ይሆናል::

9. ስልጠናና የአቅም ግንባታም በአገራችን ትክክለኛ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ እንደሆነ ተገቢ ጥናት ማካሄድ፣ ሲተገበርም የኢኮኖሚ ዋልታ ለሆኑት ለግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ አካላት የትምህርትና የስልጠና እድል እኩል ወይም በተሻለ ሁኔታ ማዳረስ፣

# የግሉ ንግድ ዘርፍ ሚና

ኃይለመስቀል አበበ
የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት ም/ዋና ጸሀፊ

## 1 መግቢያ

በኢኮኖሚ ልማትና ድህነት ቅነሳ የግሉ ንግድ ዘርፍ ሚና እጅግ ወሳኝ ነው፡፡ እያደገ የሚሄድ የግሉ ንግድ ዘርፍ የህብረተሰቡን የገቢ መጠን በማሳደግ፣ የሥራ ዕድሎች በመፍጠር እንዲሁም በተሻሻለ የጥራት ደረጃና በቅናሽ ዋጋ ምርትና አገልግሎትን በማቅረብ ለልማትና ድህነት ቅነሳ የበኩሉን አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

ከላይ እንደተጠቆመው የግሉ ንግድ ዘርፍ የሚጠበቅበትን ሚና በአጥጋቢ ሁኔታ መጫወት ይቻለው ዘንድ፣ ተስማሚ የኢኮኖሚ ፖሊሲና ስትራቴጂ መንደፍና ተግባራዊ ማድረግ፣ ፖሊሲና ስትራቴጂውን በተቀላጠፈ መልኩ፣ የሚመራና የሚያስተዳድር መንግሥታዊ አስተዳደር በመዘርጋት ምቹ ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

የተጠቀሰውን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ረገድ መንግሥት፣ መንግሥታዊ የሆኑና ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የግሉ ንግድ ዘርፍ፣ ...ወዘተ ተስማሚ የልማትና የድህነት፣ ቅነሳ ስትራቴጂ ከመንደፍ ጀምሮ እስከ አፈጻጸሙና ክትትሉ ባሉት ሂደቶች ውስጥ ተሳትፎ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

ይህ ጹሑፍ በድህነት ቅነሳ ረገድ የግሉ ንግድ ዘርፍ ሚና ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡ ጹሑፉ መግቢያውንና ማጠቃለያውን ጨምሮ በቅደም ተ ከተል ስለድህነት ገጽታዎች፣ የግሉ ንግድ ዘርፍ ባህሪና ሚና፣ የግሉ ንግድ ዘርፍ ተግባር፣ የመንግሥት የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ፣ በድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ዝግጅት የግሉ ንግድ ዘርፍ ተ ሳትፎ ያካተተ ነው፡፡

## 2 የድህነት ገጽታዎች

የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጐቶች ምግብ፣ ልብስ፣ መጠለያ፣ የትምህርትና የጤና አገልግሎቶች ናቸው፡፡ አንድ ሰው እነዚህን ፍላጐቶች በተወሰነ ደረጃ ማርካት ከተሳነው በድ-ህነት ውስጥ የሚኖር ሆኖ ይወስዳል፡፡ በአለም ባንክ መለኪያ መሠረት በቀን ከአንድ የአሜሪካን ዶላር ወይም ብር 8.50 የማያገኝ ዜጋ በፍጹም ድህነት ውስጥ የሚኖር ሆኖ ይወሰዳል፡፡ ይህም ማለት ይህ ዜጋ የተጠቀሱትን እጅግ መሠረታዊ የሆኑትን ፍላጐቶቹን የቀን ገቢው መጠን መሸፈን አያስችለውም ማለት ነው፡፡ ድህነት የተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ገጽታዎች ያሉት ከመሆኑም በላይ መንስዔዎቹም በርካታና የተለያዩ ናቸው፡፡

ከገጽታዎቹ መካከል አስተማማኝ ገቢ አለመኖር፣ የቤተሰብ ብዛት፣ ለትምህርት የደረሱ ልጆችን ወደትምህርት ቤት መላክ አለመቻል፣ የቤተሰብ አባል ሲታመም የህክምና አገልግሎት ለማግኘት አለመቻል፣ በቂ ምግብ አለማግኘት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ለድህነት እንደመንስዔ ሆነው ከሚታዩት ጉዳዮች መካከል ሥራ አጥነት፣ ከፊል ሥራ አጥነት፣ የመንቀሳቀሻ ካፒታል ዕጦት፣ ድህነትን እንደ ዕጣ ፈንታ መቀበል፣ በከፍተኛ ደረጃ እያደገ የሚሄድ የህዝብ ብዛት፣ በገበያ ተፈላጊነት ያለው ሙያ አለመኖር፣ ዝቅተኛ ምርታማነት ይገ ኙበታል፡፡

ድህነት በገጠርም ሆነ በከተማ ተንሰራፍቶ የሚገኝ ክስተት እንደመሆኑ መጠን፣ ለመቀነስ የሚደረገው ጥረት አገር አቀፍ ሽፋን ሊኖረው የሚገባና የሁሉንም ትብብር የሚሻ ነው፡፡ በድህነት ቅነሳ ረገድ ሚና የሚኖራቸው ልዩ ልዩ ተባባሪ አካላት እንዳሉ ቀደም ሲል ተ ጠቁሟል፡፡

ከድህነት ገጽታዎች መካከል ገቢ ያለመር እና ከፍጹም ድህነት የገቢ ወለል ጋር በተለይ በተ ያያዘ፣ በገቢ ማሳደግ፣ በጥራትና በቅናሽ ዋጋ ምርት/አገልግሎት ማቅረብ፣ በሥራ አጥነትና ከፊል ሥራ አጥነት ጉዳዮች ላይ የግሉ ንግድ ዘርፍ ዕንቅስቃሴ የሚያተኩር ይሆናል፡፡

## 3 የግሉ ንግድ ዘርፍ፡- ባህርይ፣ ሚና እና የተ ሳትፎ አድማስ

### 3.1 ባህሪይ

በካፒታሊስት የኢኮኖሚ ሥርዓት የግሉ ንግድ የሚሠማራበትን የሥራ መስክ ወይም የራሱን የንግድ ድርጅት ለማቋቋም የመምረጥ ነፃነት አለው፡፡ የንብረትና ዕቃ ባለቤት የመሆን፣ የመሸጥና የመለወጥ እንዲሁም ከሌሎች ሰዎች ወይም ድርጅቶች ጋር በመወዳደር ለትርፍ መሥራት ትርፍ የማግኘት ነፃነት አለው፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች በነፃ ገበያ ሥርዓት ለይ የተመሠረተ የግሉ ንግድ ዘርፍ ዓይነተኛ ባህርያት መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በነፃ የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ለትርፍ መስራትና፣ ትርፍ መሠረታዊ ጉዳይ ናቸው፡፡ ለትርፍ የሚደረግ ዕንቅስቃሴ የአንድን አገር ኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት እንዲሁም ድህነት ቅነሳ ዓላማ ዎች በሚከተሉት መንገዶች ያራምዳል፡፡

- ለትርፍ መሥራት በሰዎች ወይም ድርጅቶች መካከል ውድድር

ይፈጥራል:: በውድድሩ አማካኝነት ህብረተሰቡና ኢኮኖሚው የተሻሻሉ የዕቃዎችና አገልግሎቶች አቅርቦት በተመጣጣኝ ዋጋ ያገኛሉ::

- ትርፍ የገቢ ግብር የሚከፈልበት እንደመሆኑ መጠን፣ ለመንግሥት የገቢ ምንጭ ነው:: ይህም በጤና፣ ትምህርት ...ወዘተ ረገድ የድህነትን ጫና ለመቀነስ የሚደረገውን የመንግሥት ወጪ ለመሸፈን ያግዘዋል::
- ለትርፍ መሥራት ሰዎች በቁጠባ ያጠራቀሙትን በሥራ ላይ እንዲያውሉ/ኢንቨስት እንዲያደርጉ/ ያበረታታቸዋል:: ኢንቨስትመንት ደግሞ አዳዲስ የሥራ መስኮች እንዲፈጠሩ እንዲሁም ንግድ እንዲስፋፋ ብሎም ኢኮሚው እንዲያድግ ያስችላል::

ስለዚህም ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች በነፃ ገበያ የኢኮኖሚ ሥርዓት የግል ንግድ እንዲስፋፋ ትርፍ የላቀ የማትጋት ሚና ይጫወታል:: የንግድ ተቋማት ትርፍ የማግኘት ባህርያቸው ህብረተሰቡንና ኢኮኖሚውን እጅግ የሚጠቅሙ ተግባራት ተግተው እንዲያከናውኑ ያደርጋቸዋል::

## *3.2 ሚና*

በጥቅሉ ሲታይ የግሉ ንግድ ዘርፍ ለኢኮኖሚው ልዩ ልዩ የማምረቻ መሣሪያዎችንና ግብአቶችን እንዲሁም ለህብረተሰቡ የፍጆታ ዕቃዎችን በማቅረብ፣ ለሥራ አጥና ከፊል ሥራ አጥ አስተማማኝ የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ ለባለሀብቱ የኢንቨስትመንት መስክ ዕድል በማመቻቸት ወሳኝ ሚና ይጫወታል::

በተለይ የሥራ ዕድል ከመስጠት አኳያ የግሉን ዘርፍ ሚና ለማሳየት እንዲቻል «እ.አ.አ. 1999 ዓ.ም. በሥራ ላይ የነበሩ ሰዎች ብዛት በኢትዮጵያ:- በሥራ ሥምሪት፣ በአገር፣ በገጠርና በከተማ» በሚል ርዕስ ሠንጠረዥ ከዚህ ጽሁፍ ጋር ተያይዞ ቀርቧል:: ከሠንጠረዡ ለመረዳት እንደሚቻለው እ.አ.አ. በ1999 ዓ.ም. በሥራ ላይ ለነበሩ ሰዎች የሥራ ዕድሉን በመስጠት በአገር፣ በገጠርና በከተማ በቅደም ተከተል ከጠቅላላው የሥራ ሥምሪት ከመቶ 95.67፣ 97.83፣ 78.78 የላቀ ድርሻ ያበረከተው የግሉ ዘርፍ ሲሆን፤ በተመሳሳይ ሁኔታና ቅደም ተከተል ከመቶ 2.94፣ 1.04 እና 17.79 ድርሻ በማበርከት በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኘው የመንግሥት የሥራ መስክ (የመንግሥት ተቀጣሪና የልማት ድርጅቶች ሠራተኞች) ነው::

የሠንጠረዡ ሌላው ገጽታ የራሱን ሥራ የሚሠራ ድርሻ በገጠር፣ በከተማ እንዲሁም በአገር ደረጃ ከመቶ 42.22 እስከ 43.70 በሚደርስ ከፍተኛውን ቦታ መያዙ ነው::

እንዲሁም ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ በከተማ የሥራ ሥምሪት ረገድ የራሱን ሥራ የሚሠራ ከጠቅላላው የሥራ ስምሪት በመቶ 42.22 ድርሻ በመያዝ ከፍተኛውን ሚና የሚጫወት ሲሆን፣ በክፍያ የግል ድርጅት ሠራተኛና የመንግሥት ሠራተኛ በቅደም ተከተል በመቶ 19.60 እና 17.79 ድርሻ በመያዝ ጉልህ ሚና አላቸው:: ይህም በወደፊት የግሉ ዘርፍ ሚና በአገር ደረጃ የራሱን ሥራ የሚሠራ እና በክፍያ የግል ድርጅት ሠራተኛ ሚና የጐላ ሊሆን እንደሚችል ነው::

የግሉ ንግድ ዘርፍ ምርታማነትን በማሳደግና የሥራ ዕድል በመፍጠር ድህነትን ለመቀነስ ወሳኝ ሚና መጫወት የሚቻለው በግል ተነሳሺነት፣ የንግድ ፕሮጀክት ሀሳብ በማመንጨት፣ መዕዋለንዋይ በማፍሰስ፣ ቴክሎጂ በማሰራጨት ነው::

## *3.3 የተሳትፎ አድማስ/ትኩረት*

የድህነት ቅነሳ ዕንቅስቃሴ ውስጥ የግሉ ንግድ ዘርፍ ተሳትፎ መሠረታዊ ባህሪዩን ማለት ለጥረቱ ተመጣጣኝ ትርፍ የማግኙቱን አስፈላጊነት ባገናዘበ መልኩ፣ የንግድና ኢንቨስትመንት ዕንቅስቃሴውን በማስፋፋት በኢኮኖሚውና በህብረተሰቡ ተፈላጊ የሆኑትን ምርቶች/አገልግሎቶች በሚፈለገው የጥራት ደረጃ፣ መጠንና ዋጋ ማቅረብ የሚችሉ የንግድ ተቋማትን መገንባት፣ ማካኼድና ማስፋፋት ነው:: የነዚህ ተቋማት መገንባትና መስፋፋት ለኢኮኖሚ ዕድገትና ለሥራ ዕድል መፈጠር አስተማማኝ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ::

ከላይ ከተመለከተው የተሳትፎ አድማስ ጐን ለጐን የምርምርና ስርፀት ተግባር ማከናወን፣ ተስማሚ ቴክኖሎጂ ወደሀገር ውስጥ ማስገባትና ከሀገር ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እንዲጣጣም ማድረግ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያገኙ መልካም የሥራ አመራር ስልቶችን መተግበር፣ እንደሁም ተስማሚ የገበያ አውታር መዘርጋት ይጠበቅበታል:: ይህም ቀጣይነት ላለው የኢኮኖሚና የቴክኖሎጂ ልማት እንዲሁም ድህነት ቅነሳ ዕንቅስቃሴ በራሱ ውስጣዊ ኃይል

የሚመራና እየተስፋፋ የሚሄድ ጠንካራ የግል ንግድ ዘርፍ ለማልማት መሠረት ነው:: በመሆኑም በዚሁ መንፈስ የግሉ ንግድ ዘርፍ እንዲጐለብት የሚያስችሉ የፖሊሲና ድጋፍ ፕሮግራሞች በመቀየስ እንዲሁም ቀልጣፋ አስተዳደር በመዘርጋት ረገድ የድህነት ቅነሣው ስትራቴጂ ዝግጅት ሊያተኩርባቸው የሚገባ ጉዳይ ናቸው:: ለዚህም የግሉ ንግድ ዘርፍ በተጠሪዎቹ አማካኝነት አስተያየቱን የሚሰጥበት ኦፊሲየል መድ ረክ ሊፈጠርለት ይገባል::

### *4 በድህነት ቅነሣ የግሉ ንግድ ዘርፍ ተግባር*

ድህነት በገጠርና በከተማም ተንሰራፍቶ የሚገኝ እንደመሆኑ መጠን፣ ለመቀነስ የሚደረገው ጥረት ወይም ዕንቅስቃሴ አገራዊ ሽፋን ሊኖረው ይገባል:: የግሉ ንግድ ዘርፍ ተሳትፎ ይህንኑ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ዕንቅስቃሴውን መምራት ይጠበቅበታል:: በዚህ ረገድ የግሉን ንግድ ዘርፍ ተግባራት በገጠርና በከተማ በመለየት ቀጥሎ ለመጠቆም ተሞክሯል::

#### *4.1 ድህነት ቅነሣ በገጠር*

በገጠር ድህነትን የመቀነስ ተግባር የግብርናውን ዘርፍ ከገበያ ፍላጐት ጋር በተያያዘ መልኩ ምርታማነት ከማሳደግ፣ የገጠሩን ነዋሪ የገቢ ምንጭ በማስፋት ገቢውን ከፍ ከማድረግ፣ የተመጣጠነ የገቢ ስርጭትና የተሻሻለ የኑሮ ሁኔታ ከማስገኘት አኳያ በተለይ የራሱን ሥራ የሚሠራ እንዲሁም ያለክፍያ የቤተሰብ አባል ሠራተኛ ላይ ማተኮር የሚጠበቅበት ሊሆን ይገባል::

ለገጠር ድህነት መስፋፋት እንደ መንስዔ ተደርገው ከሚወሱት ጉዳዮች መካከል አፈር ለምነቱን ማጣቱና መሸርሸሩ፣ ከምግብ አቅርቦት ጋር ያልተ መጣጠነ ከፍተኛ የህዝብ ዕድገት፣ የማገዶ ዕጥረት፣ የምርት መበራከትና የገበያው ፍላጐት አለመዛመድ የሚጠቀሱ ናቸው:: እነዚህን ጉዳዮች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የግሉ ንግድ ዘርፍ ውጤታማ ሊሆን በሚችልባቸው በተለይ በሚከተሉት አቅጣጫ ኢንዲሳተ ፍ ሁኔታዎች ሊመቻቹለት ይገባል::

- የማገዶ አንጨትን የሚተኩ ቴክኖሎጂዎችን ማልማትና ማሰራጨት፣
- በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ገበያዎች ተፈላጊት ያላቸውን የግብርና ምርቶች ምርታማነት በመጨመር የገበሬውን የገቢ መጠን ለማሳደግ፣
- የተሻሻለ የሰብል አያያዝ በገበሬ ዘንድ እንዲሰርጽ ለመጣር፣
- ልዩ ልዩ የግብርና ግብአቶች ያለምንም ገደብ ለገበሬው በማቅረብ የምርቱን መጠን ለማሳደግ፣

ከላይ በተዘረዘሩት መሠረት የግሉ ንግድ ዘርፍ መሳተፍ ይቻለው ዘንድ፣ ለገበሬው አስፈላጊ የግብርና ግባአቶችን የሚያቀርብ እንዲሁም ከገበሬው ምርቱን ተቀብሎ ወደሚፈለግበት የሀገር ውስጥና የውጭ ገበያ የሚያደርስ ቅንጅት ያለው የእርሻ ገበያ ተቋም እንዲፈጥርና አንዲያለማ ሁኔታዎች ሊመቻቹለት እንደሁኔታውም የድጋፍ ፕሮግራም ሊዘረጋለት ይገባል:: እነዚህ ተቋማት ለገበሬው በሚከተለው አኳኋን ግልጋሎት ይሰጡታል::

- የእርሻ ግብአቶችን በወቅቱና በተ ወዳዳሪ ዋጋ እንዲያገኝ፣
- ገበሬው ከፍጆታው በላይ ለሚያመርተው በተረጋጋ ዋጋ አስተ ማማኝ ገበያ ለመፈለግና ለማግኘት፣
- ለገበሬው ወቅታዊና ተስማሚ የሆነ የመረጃ ድጋፍ በመስጠት፣
- በምርምርና ስርፀት አማካኝነት የምርጥ ዘር ለተወሰነ ቦታ ተስማሚ መሆኑን በመስክ በማረጋገጥ ማሰራጭት፣

የግሉ ንግድ ዘርፍ ሊሳተፍባቸው የሚችሉ ከላይ የተጠቀሱት መስኮች የ ረጅም ግዜ የልማት ዕንቅስቃሴዎች እንደመሆናቸው መጠን፣ የግሉ ንግድ ዘርፍ ኢንቨስት እንዲያደርግባቸው የሚበ ረታታበት ሁኔታ ሊፈጠርለት ይገባል::

መንግሥትና ዓለም አቀፍ ለጋሽ ሀገሮች የግሉ ዘርፍ በተጠቀሱት መስኮች በተለይ በምርምርና ስርፀት እንዲሳተፍ ዓቅሙን ሊያጐለብቱለት እንዲሁም ተሳትፎውን እንዲስቡ እንደሁኔታው ቀጥታ የገንዘብ ድጐማና በአነስተኛ ወለድ ብድር የሚያገኝበት ሊመቻች ይገባል::

በገጠር ልማት ብቻ ለሠፊው የገጠር ሕዝብ በሚፈለገው መጠን የገቢውን ደ ረጃ ማሻሻልና የሥራ ዕድል መፍጠር የሚቻል ሆኖ አይገመትም:: የግሉ ንግድ ዘርፍ በገጠር በሚያደርጋቸው የንግድ ዕንቅስቃሴዎች ጭምር በሚፈጠሩ የሥራ ዕድሎች በላይ የሚሆነው የገጠር ሥራ አጥ ወደ ከተማ በመፍለስ፣ ሥራ የመፈለግና ኑሮውን የመመስረት ሂደት

ቀጣይነት የሚኖረው እንደሚሆን ይታሰባል።

## 4.2 ድህነት ቅነሣ በከተማ

ከገጠር ወደ ከተማ የሚፈልሰው ሥራ ፈላጊ እንዲሁም የከተማው ሥራአጥ ተ ዳምረው፣ የከተማ ሥራ አጥ ቁጥር እየጨመረ የሚሄድ መሆኑ እርግጥ ነው። የግሉ ንግድ ዘርፍ በልዩ ልዩ የንግድ ዘርፎች ሠፊ መዋዕለንዋይ በማፍሰስ የሥራ ዕድል እንዲከፍት እንዲሁም የራሱን ሥራ የሚሠራ እንዲበረታታ ሁኔታዎች ሊመቻቹለት ይገባል። ኢንቨስትመንት ቁጠባ ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ መጠን፣ የሀገር ውስጥ ቁጠባ ለሚፈለገው የኢንቨስትመንት መጠን የሚመጥን ስለማይሆን፣ የሌሎች ሀገሮች ኢንቨስትመንት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲሳብ ማትጋት ያስፈልጋል።

የግሉ ንግድ ዘርፍ የመቆጠብ አቅሙ እንዲጐለብት፣ በሚያገኘው ተመጣጣኝ ትርፍ ተበረታትቶ በቁጠባ ያከማቸውን መዕዋለንዋይ ኢንቨስት እንዲያደርግ እንዲሳብ የታክስ ሥርዓቱ፣ ንግድና ኢንቨስትመንትን የሚደግፍና የሚያበ ረታታ የኢኮኖሚ ፖሊሲ፤ ፖሊሲውን ማስፈጸሚያ ህጐች ደንቦችና መመሪያ ዎች እንዲሁም አስፈጻሚ ተቋማትና ቀልጣፋ የአሠራር ስርዓት የንግድ ሥራን በዝቅተኛ ወጪ ለመስራት በሚያስችል ይዘታቸው ተቀነባብረው እንዲቀርቡ ይጠበቃል።

በጥቅሉ ሲታይ የግሉ ንግድ ዘርፍ በገጠርም ሆነ በከተማ የሥራ ዕድል የሚከፍቱ የልማት ፕሮጀክቶችን ተ ግባራዊ በማድረግ፣ ለድህነት ቅነሣ ስትራቴጂ ተፈጻሚነት የበኩሉን ድርሻ መወጣት የሚችል ነው። ይሁንና ድርሻውን ማበርከት ይቻለው ዘንድ፣ በመንግሥት መቅረብ የሚገባቸው መሠ ረተ-ልማቶች እንደ መንገድ፣ ኤሌክትሪክ ኃይል በከፍተኛ ደረጃ ማመንጨት፣ ...ወዘተ የግል ንግድና ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታ ፖሊሲና የድጋፍ ፕሮግራም ተሟልተው መገኘት ይኖርባቸዋል።

# 5 የመንግሥት የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ

መንግሥት ጊዜአዊ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ PRSP ረቂቅ ሰነድ አዘጋጅቶአል። ይህ ሰነድ አገሪ ቱ ከፍተኛ የውጭ ብድር ያለባት ድሃ አገር በመሆንዋ ለዕዳ ቅነሳና ተጨማሪ የውጭ ብድር ለማግኘት ብቁ ለመሆን ማዘጋጀት ያለባት ሲሆን፣ ተቀባይነቱም ነፃ ንግድን ከመገንባት ጋር የተቆራኘ ሊሆን እንደሚችል ይታመናል። ሰነዱ ካተኮረባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል የግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ፣ የዳኝነትና የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻል ላይ እንዲሁም የሰነዱ ተ ቀባይነት ከነፃ ንግድ ግንባታ ጋር ቁርኝት ያለው ቢሆን ስለእንድምታው አስተያየቴን ቀጥዬ አቀርባለሁ።

## 5.1 የግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ

### 5.1.1 የፖሊሲው ይዘት

ፖሊሲው ገጠርንና ገበሬውን ማዕ ከል ያደረገ ነው። በፖሊሲው መሠረት የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት መነሻ ግብርና ሆኖ የመጨ ረሻ ግቡ የኢንዱስትሪ ልማት ነው። የግብርናው ዘርፍ ለኢንዱስትሪ ልማት የካፒታልና የጥሬ ዕቃ ምንጭ ብቻ ሳይሆን በሀገር ውስጥ ለኢንዱስትሪ ምርት የገበያ መሠረት በመሆን የሚያገለግል ነው። በሌላ አነጋገር በፖሊሲው መሠረት የግብርናው ዘርፍ በአገር ውስጥና በዓለም ዓቀፍ ገበያዎች አማካኝነት ለአገሪ ቱ የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት እንደሞተር ሆኖ የማንቀሳቀስ ሚና መጫወት የሚጠበቅበት ነው። ፖሊሲው የአገሪቱ የረዥም ጊዜ የኢኮኖሚ የዕድገትና ልማት መመሪያ እንደመሆኑ መጠን የሚከተሉትን ሁኔታዎች በተ ጨማሪ ትኩረት ሊሰጥ ይገባዋል እላለሁ።

### 5.1.2 ለኢንዱስትሪና አገልግሎት የኢኮኖ ሚ ዘርፎች ከመነሻው ትኩረት መስጠት

የግብርናው ዘርፍ በፖሊሲው መሠረት ከላይ የተመለከተውን ሚናውን በአግባቡ እንዳይጫወት የሚከተሉት ሁኔታዎች ይገድቡታል የሚል አመለካከት አለኝ።

- የገጠሩ ነዋሪ ሕዝብ ብዛት በከፍተኛ ፍጥነት እየጨመ ረ መሄድ የእርሻ መሬት ድልድልን ተደጋጋሚ የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ፣ በተከታታይ ድልድሎች የሚደርስ የእርሻ መሬት መጠን መቀነስ ለገበያ ቀርቶ

ለራስ ፍጆታ በቂ ማምረት አለመቻል፣

- የተለመዱት የእርሻ ምርቶች /ጤፍ፣ በቆሎ፣ ገብስ፣ ስንዴ ...ወዘተ/ በዓለም ገበያ ተቀባይነት የማግኘ ታቸው·ና ተወዳዳሪ የመሆናቸው ዕድል ውሱን መስሎ ስለሚታይ፣

- በከፍተኛ ደረጃ ከሚጨምር የእርሻ ምርት አኳያ የሀገር ውስጥ ገበያ ጠባብ መሆን፣

ከላይ ለመጠቆም እንደተሞከረው የግብርናው ዘርፍ ልማቱን ከሚገቱት ሁኔታዎች አንፃር የአገሪቱን የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት በሚፈለገው መጠንና ፍጥነት ማራመድ ይሳነዋል የሚል ስጋት አለኝ:: ስለዚህም ፖሊሲው እንደሁኔታው ለኢንዱስትሪ ልማትና አገልግሎት ማስፋፋት እንዲሁም ለግብርና ልማት ሚዛናዊ ትኩረት ቢሰጥ የኢኮኖሚ ዕድገት በማምጣትና ድህነትን በመቀነስ አቅጣጫ የሚደረገውን ዕንቅስቃሴ ይበልጥ ያራምደዋል:: ይህም ማለት የኢንዱስትሪው ልማት ከግብርና በሚገኙ ምርቶች በጥሬ ዕቃነት በመጠቀም ላይ ሳይወሰን እንደአግባብነቱ በእርሻ ላይ ያልተመሰረቱ የኢንዱስትሪና የአገልግሎት የኢኮኖሚ ዘርፎችን ከመነሻው እንዲያካትት ሆኖ እንዲነደፍ ማድረግ አስፈላጊ ነው::

የኢንዱስትሪ ልማት የአንድን ሀገር ኢኮኖሚ ልማት እንደሞተር ሆኖ የማንቀሳቀስ ሚና ይጫወታል:: ይህንኑ ሚናውን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣ የአንድ አገር የልማት ጥረት ስኬት ከሚመዘንባቸው አንዱ መንገድ የእርሻ ኢኮኖሚውን ወደ ዘመናዊ የኢንዱስትሪ ኢኮኖሚ ማሸጋገር ወይም መለወጥ መቻሉ ነው:: በመሆኑም የኢንዱስትሪ ልማት ጠቅላላ ኢኮኖሚውን እንደሞተር ሆኖ ለማሳደግ ያለውን ኃይል በመገንዘብ፣ እንደአግባብነቱ በሁሉም የኢንድስትሪ መስኮች የልማት ዕንቅስቃሴ የሚበረታታና የሚደገፍ ስለመሆኑ በልማት ፖሊሲው ትኩረት ሊሰጠው ይገባል::

### *5.1.3 በተጨማሪ ለሚመረተው የእርሻ ምርት አግባብነት*

የእርሻ ልማት ስትራቴጂው የምርት መጠንና ምርታማነትን በማሳደግ ላይ ያተከረ መሆኑ ግልጽ ነው:: ግልጽ ሆኖ ያልተ መለከተው ግን በተጨማሪ የሚመረተው ምርት አግባብነት ማለት በሀገር ውስጥም ሆነ በዓለም ገበያዎች ያለው ተፈላጊነትና ተቀባይነት ነው:: በመሆኑም የሚመረተው ምርት ለማን ነው የሚለው ጥያቄ መልስ ሊያገኝ ይገባል::

ከገበሬው ፍጆታ በላይ የሆነ ምርት ለሀገር ውስጥ ገበያ ቀርቦ የሚሸጥ መሆን ይኖርበታል:: በሌላ በኩል ከሀገር ውስጥ ፍጆታ በላይ የሚሆነው በውጭ ሀገር ገበያዎች የሚፈለግና በጥራትም በዋጋም ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል:: ስለዚህም መሠረታዊ የሆኑት የእርሻ ምርቶች መጠን ዕድገት ከአገር ውስጥና ከውጭ ገበያዎች ፍላጐት አኳያ መታየት ይኖርበታል:: የሀገር ውሰጥ ገበያውን በማስፋት ረገድ የሚደረግ የእርሻ ምርት የማሳደግ ዕንቅስቃሴ በአካባቢ ስፔሻላይዜሽን ላይ አተኩሮ ገበሬው ራሱ የግብርናው ምርት ገበያ አካል እንዲሆን የሚያበረታታ የማትጊያ ሥርዓት በፖሊሲው መካተት ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ሆኖ ይሰማኛል::

### *5.1.4 ለቴክኖሎጂ ዓቅም ግንባታ*

በተወሰኑ የኢንዱስትሪ መስኮች የኢንዱስትሪ ቴክኖሎጂ ዓቅም መገንባት ጉዳይ አልተመለከተም:: የኢንድስትሪ ልማት ከቴክኖሎጂ ዓቅም ግንባታ ጋር መያያዝ ያለበት ነው:: ስለዚህም ከልማት ራዕይ አኳያ በሚመረጡ የቴክሎጂ ልማት ዕንቅስቃሴዎች ለምሳሌ፣ የእርሻ መሣሪያዎች ከአገር ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞና አሻሽሎ ለመሥራት በሚደረጉ ሙከራዎች ላይ ያነጣጠረ የማበረታቻና የድጋፍ ፕሮግራም አስፈላጊነት በፖሊሲ ሊመለከት ይገባል::

### *5.1.5 ለቴክኖሎጂ ስርጭት*

በግል ተነሳሺነትና በግል ንግድ ተቋም አማካኝነት ለገበሬው ግብአቶች እንዲሁም ከገበሬው ምርት ተቀብሎ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ የማቅረብ ተገቢነት በስትራቴጂው ተመልክቷል:: ይሁንና ከዚሁ ግንኙነት ጋር በተያያዘ ለገበሬው በምርምርና ስርፀት አማካኝነት የሚገኝ የገበያና የግብርና ቴክኖሎጂና መረጃ የሚያሰራጩ የግል ንግድ ተቋማት እንዲቋቋሙ ወይም እንዲበረታቱ የድጋፍ ፕሮግራም በግልጽ በፖሊሲው ትኩረት ሊሰጠው ያስፈልጋል::

## *5.2 የዳኝነትና የሲቪል ሰርቪስ አሠራር ማሻሻል*

የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂው ለዳኝነትና ሲቪል ሰርቪስ መሻሻል ማለት መልካም አስተዳደር በመዘርጋት፣ ግልጽነትና ተጠያቂነትን በማስፈን ረገድ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቷል:: የግሉ ንግድ ዘርፍ የንግድ ዕንቅስቃሴውን ማለት የንግድ ተቋም መገንባት፣ ማካሄድና ማስፋፋት ተግባሩን በአነስተኛ ወጪ መምራት ይጠበቅበታል:: ይህም በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የሚገጥመውን ውድድር ለመቋቋም የሚያደርገውን ጥረት በእጅጉ የሚደግፍ ይሆናል:: ስለሆነም ቀልጣፋ የአስተዳደር ስልት ከመዘርጋት፣ ሙስናን ከመቆጣጠር፣ በህገ መንግሥቱ መሠረት የዳኝነት ህጐችን በመለወጥ ...ወዘተ አኳያ የሚወሰዱ የዳኝነትና ሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ እርምጃ የንግድ ሥራን በአነስተኛ ወጪ ለመምራት የበኩላቸውን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ስለሚያደርጉ የተሰጠው ትኩረት አግባብ ነው:: እዚህ ላይ በማሻሻሉ ሂደት የግሉ ንግድ ዘርፍ ተሳትፎ አስፈላጊ ነው::

## *5.3 የነፃ ንግድ ግንባታ*

ድሃ አገሮች የሚያዘጋጁት የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ተቀባይነት አግኝቶ የዕዳ ቅነሳና ብድር ማግኘት እንዲችሉ፣ ነፃ ንግድ እንዲገነቡ የሚገደዱ ቢሆን እንድምታው በአግባቡ ሊጤን ይገባል::

በመሠረቱ ነፃ ንግድ በውድድር አማካኝነት ህብረተሰቡና ኢኮኖሚው የተሻሻሉ የዕቃዎችና አገልግሎቶች አቅርቦት በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ የሚያስችል በመሆኑ የሚደገፍና አገሮች ሊያራምዱት የሚገባ ነው:: ይሁንና በኢንዱስትሪና በቴክኖሎጂ ልማት እጅግ ወደፊት የገፉት አገሮች በልማታቸው እጅግ ኋላቀር ከሆኑት ጋር በአንድ ገበያ ውስጥ ከወዲሁ በእኩል ይወዳደሩ ማለት በድሃ አገሮች በጅማሮ ላይ ያሉ የኢንዱስትሪ ተቋማትን የሚያከስም እንዲሁም አዳዲስ እንዳይገነቡ መሰናክል ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለ::

ስለዚህ የድሃ አገሮች ኢንዱስትሪ የነፃ ገበያ ውድድርን መቋቋም እንዲችል የመወዳደር ብቃቱ እንዲጐለብት ለማድረግ በቂ የመሸጋገሪያ ጊዜ ሊሰጠው ይገባል የሚል አስተሳሰብ አለ:: ስለሆነም የነፃ ንግድ ግንባታ ከድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ተቀባይነት ጋር ከወዲሁ የተቆራኘ ከሆነ፣ ለግሉ የኢንዱስትሪ ዘርፍ መክሰም ብሎም ልማት መደናቀፍ ሊከሰት ይችላል የሚል ስጋት አለ::

## 6 በድህነት ቅነሣ ስትራቴጂ ዝግጅት ተሳትፎ

ለዕድገትና ልማት ምቹ ፖሊሲ ለመፍጠር እንዲሁም የተፈጠረው ፖሊሲ በየጊዜው የሚለዋወጡ ሁኔታዎችን በተቻለ ፍጥነት እንዲያገናዝብ ለማድረግ እንዲቻል በመንግሥትና በግሉ ንግድ ዘርፍ መካከል ቋሚና በተወሰነ ጊዜ የመገናኛ መድረክ መፍጠር ያስፈልጋል:: ይህ መድረክ ባለመኖሩ መንግሥት ለሚነድፈው ፖሊሲ አስፈላጊ ግብአት አያገኝም እንዲሁም ነጋዴው ለወደፊት ዕቅዱ መረጃ አያገኝም::

በድህነት ስትራቴጂ ዝግጅት የግሉ ዘርፍ የሚሳተፍበት መድረክ የሚፈጠር መሆኑ ከጊዜአዊ የድህነት ስትራቴጂው ለመገንዘብ ተችሏል:: ይህ መድረክ የመንግሥትን የዕድገትና የልማት ዓላማዎች የሚያሟሉና የግሉ ንግድ ዘርፍ የንግድ ተቋማት ለመገንባት፣ ለማካሄድና ለማስፋፋት የሚያደርገው ዕንቅስቃሴ በአነስተኛ ወጪ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን የሚያስችሉ ፖሊሲና ስትራቴጂ መንደፍ ያስችላል የሚል አስተያየት አለኝ::

የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት በዚህ መድረክ ላይ ንቁ ተሳትፎ ለማድረግ ይቻለው ዘንድ ከግል ንግድ ዘርፍ ዕይታ አኳያ የድህነት ቅነሣ ስትራቴጂን መርምሮ ስለይዘቱና የነጋዴው ተሳትፎ አስተያየቱን የሚያቀርብ ከነጋዴው የተውጣጣ ኮሚቴ ሰይሞ ሥራውን ጀምሯል:: የኮሚቴው የሥራ ውጤት በድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ዝግጅት ሂደቶች ማለት የድህነት መንስዔዎችን መርምሮ ከመለየት ጀምሮ፣ ተስማሚ ፖሊሲና ስትራቴጂ መንደፍ፣ ፕሮግራም ዝግጅት፣ የአፈጻጸም መርሀ-ግብር ለተጠያቂነት ማመቻቸት እስከ አፈጻጸምና ውጤት ግምገማ የንግድ ምክር ቤቱ ለሚያደርገው ተሳትፎ አቅጣጫ የሚያስይዘው ይሆናል::

## 7 ማጠቃለያ

የግሉ ንግድ ዘርፍ በሚያቋቁማቸው፣ በሚያካሂዳቸውና በሚያስፋፋቸው የንግድ ተቋማት አማካኝነት ሀብት ይፈጥራል፣ የዜጎች ገቢ ያሳድጋል፣ የሥራ ዕድሎች ይፈጥራል:: በዚህም ዕንቅስቃሴው ድህነትን በመቀነስና የኢኮኖሚ ዕ ድገትን በማስገኘት የበኩሉን አስተዋጽኦ ያበ ረክታል::

ዕንቅስቃሴው ውጤታማ ይሆን ዘንድ፣ የሚነደፉ ፖሊሲዎች፣ ህጐችና ደንቦች አስተ ዳደራዊ መዋቅሮችና የአሠራር ሥርዓቶች የንግድ ሥራ ለማከናወን የሚጠይቀው ወጪ ከሌሎች አገሮች አኳያ ያለአግባብ እንዳይንር በዝቅተኛ ደረጃ እንዲያዝ ማስቻል ይጠበቅባቸዋል::

ኢኮኖሚን ለማሳደግና ድህነትን ለመቀነስ የሚነደፍ ፖሊሲና ስትራቴጂ የንግድ ሥራ በአነስተኛ ወጪ እንዲከናወን የሚያስችል እንዲሆን፣ የግሉ ንግድ ዘርፍ በተጠሪዎቹ አማካኝነት በሚመቻቹ የመንግሥትና የልማት ተ ባባሪዎች የውይይት መድረኮች ላይ ለመሳተፍ ዝግጁ ነው::

*ኢ.ፌ.ዴ. በ1999 ዓ.ም. በሥራ ላይ የነበረ ሰዎች ብዛት በኢትዮጵያ፡-*
*በሥራ ስምሪት፣ በአገር፣ በከተማና በገጠር ደረጃ*

| ተራ ቁ | የሥራ ስምሪት | በአገር | በከተማ | በገጠር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በሥራ ላይ የነበሩ ስዎች ብዛት /በቁጥር/ | 25,073,412 | 2,879,303 | 22,194,109 |
| 2 | የሥራ ስምሪት /ከመቶ/ (Employment Status %) | 100 | 100 | 100 |
| 2.1 | የግሉ ዘርፍ (Private Sector) | 95.67 | 78.78 | 97.83 |
| | ♦ አሠሪ ባለንብረት (Employer) | 0.78 | 0.96 | 0.75 |
| | ♦ በክፍያ የግል ድርጅት ሠራተኛ (Employee Private Organization) | 4.34 | 19.60 | 2.35 |
| | ♦ የራሱን ሥራ የሚሠራ (Self-employed) | 43.53 | 42.22 | 43.70 |
| | ♦ ያለክፍያ የቤተሰብ አባል ሠራተኛ (Unpaid Family Worker) | 46.93 | 15.53 | 51.00 |
| | ♦ አፕሬንቲስ (Apprentice) | 0.05 | 0.31 | 0.01 |
| | ♦ የህብረት ሥራ ማህበር ሠራተኛ (Member of Cooperative) | 0.04 | 0.16 | 0.02 |
| 2.2 | የመንግሥት ሠራተኛ (Employee Gov-ernment) | 2.94 | 17.79 | 1.04 |
| | ♦ የመንግሥት ተቀጣሪ (Employee Government | 2.40 | 15.37 | 0.75 |
| | ♦ የልማት ድርጅቶች ሠራተኛ (Employee Parasatal) | 0.54 | 2.42 | 0.29 |
| 2.3 | የሌሎች ድርጅቶች ሠራተኛ (Others Paid Employees) | 0.90 | 2.06 | 0.75 |
| 2.4 | ሌሎች ሠራተኞች (Others) | 0.33 | 1.19 | 0.22 |
| 2.5 | ያልተገለጹ (Not stated) | 0.14 | 0.16 | 0.14 |

ምንጭ:- የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን እ.አ.አ. የ1999 ዓ.ም. ብሔራዊ የሰው ኃይል ቅኝት በእንግሊዝኛ ካዘጋጀው ስታቲስቲካዊ ሪፖርት እ.አ.አ. ማርች 1999 ቡለቲን ቁጥር 225 ላይ የተቀነባበረ

# አጠቃላይ ውይይት

## የመጀመሪያው ዙር ውይይት

1. ድህነት ቅነሳ እና ሀብት ማካፈል በእርግጥ ሁለቱም ሊነጣጠሉ አይችሉም:: ሀብት ማካፈል ማህበራዊ ኃላፊነትና ሀገራዊ ኃላፊነትንም የያዘ ነው:: ሀብት የሚጨምረው ከማካፈል ጋር ነው:: ለእኔ ቀጥተኛ ትርጉሙን እንደዚሁ በማካፈል ብቻ ከወሰድነው በዛ ሊያስኬድ ይችላል:: ግን ማኅበራዊ ኃላፊነት ከሌለ የድህነት ቅነሳውም አይኖርም:: ስለዚህ ያው ሀብት መጨመሩና ሀብት ማካፈሉ በአንድ ላይ እንዲታዩ ቢደረግ ጥሩ ነው ለማለት ፈልጌ ነው:: ሌላው በእርሻውና በኢንዱስትሪው በኩል እኩል ትኩረት ሊሰጥ ይገባል የሚለው ሀሳብ እጅግ በጣም ያስቸግራል:: ከኢኮኖሚ ፖሊሲና ስትራቴጂ ሲነሳ የሚታዩ የተለያዩ መስፈርቶች ይኖራሉ:: ያለው ነባራዊ ተጨባጭ ሁኔታ ምንድነው? ያለን አቅም ምንድነው? አሁን ያለው የሰው ኃይል ሙያ ወ.ዘ.ተ… የሚባሉ ነገሮች ሲመጡ የግድ ትኩረት ለሁሉም ሊሰጥ ይገባል:: እኩል ትኩረት ለመስጠት ግን ሊያዳግት ይችላል:: ይኼን ሀሳብ ጠቆም ለማድረግ ያህል ነው::

2. እኔ የምጠይቀው የግሉ ኢኮኖሚ መዳበር በተለይ ስራ በመፍጠሩ በኩል ትልቅ አስተዋፅዖ እንዳለው ሁላችንም የምናውቀው ነው:: አሁን ከፅሑፉ እንደተረዳሁት ግን የግሉ ኤኮኖሚ ስራ ከመፍጠር ይልቅ እራሱ ሊጠፋ የደረሰበት ሁኔታ አለ እና ተጠያቂው ፖሊሲውና ሌሎች ሌሎች ነገሮች ናቸው ሲባል የሰማሁ መሰለኝ:: በእርግጥ የፖሊሲ ችግር ሊኖር ይችላል:: ሁላችንም የምናውቀው ነው:: በመንግስት አካባቢ የሚታዩ ችግሮች ግልፅ ናቸው:: እራሱ የግል ሴክተሩ ለዚህስ እራሱ ተጠያቂ አይደለም ወይ? ማለት እንደሌሎች አገሮች የግል ሴክተሩ ተጠናክሮ ኅብረት ፈጥሮ ካፒታሉን በጋራ አቀናጅቶ ማኔጅመንቱን በጋራ አቀናጅቶ በመስራት በኩል እኛ አገር ያለ ባለሀብት ምን ያህል ብቁ ነው? እራሱን ምን ያህል ፈትሿል? ማለት ችግሮችን ሁልጊዜ ኤክስተርናላይዝ (Externalize) እያደረግን ወደመንግስት እያሳበብን ነው:: መንግስት የራሱን ድርሻ ይወስዳል:: መንግስት፣ ፖሊሲ የሚያወጣው፣ ህግ የሚያወጣው አካል፣ የራሱ ችግሮች አሉበት እናም እሱ የራሱን ድርሻ ይወጣል:: የግል ባለሀብቱስ እንዴት ነው እዚህ አካባቢስ እራሱን ፈትሿል ወይ? ሁልጊዜ እኛ ጋር ያለው ችግር ባለሀብቱ ራሱ ጋር ያለውን ችግር ማየት ካልቻለ ነገም ከነገ ወዲያም ችግሩ የሚፈታ አይመስለኝም:: ታግሎ ለመወጣት እራሱን በማቀናጀት በማስተባበር በዚህ ረገድ ያለው ችግር እንዴት ነው? ብዙውን ጊዜ እንደዚህ ዓይነት ነገር ስለማልሰማ ነው ሁልጊዜ ወደ ፖሊሲ ወደ ምናምን ስለሚሳበብ በዚህ አካባቢ ያለውን ችግር አይታችኋል ወይ?

3. አቶ ብርሃነ መዋን ላመሰግናቸው እፈልጋለሁ:: ምክንያቱም በስፋቱም በጥልቀቱም ብዙ ቁም ነገር ያለው ነገር ነው ያካፈሉን:: እንዲያውም አንዳንድ ቦታዎች ስለ PRSP (በአማርኛው የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም) ብዙ ካየኋቸው፣ ከሰማኋቸው ውይይቶች በጣም የተሻለ ሆኖ ነው ያገኘሁት:: ከሞላ ጎደል ብዙ በተናገሩት ነገር ላይ እኔም እስማማለሁ አንዳንድ ምን አልባት ለየት ያሉ ጥያቄዎች ቢኖሩም ላነሳቸው አልፈልግም ብዙ አስቸጋሪዎችም ሊሆኑ ይችላሉ:: ብዙ አነጋጋሪ አከራካሪ ሊሆኑ ይችላሉ:: ለምሳሌ ቅድም በአንድ ተናጋሪ እንደተጠቀሰው የእርሻውና የኢንዱስትሪው መመጣጠን የሚባለው ነገር ነው:: ለምሳሌ እሱ በጣም አስቸጋሪ ጉዳይ ነው:: እኔ ላነሳው የምፈልገው እሳቸው ጠቆም ባደረጉት ላይ ትንሽ ለማከል ነው:: እሳቸው እንዳሉት ድህነትን ለመቀነስ መታገል ፍፁም አስፈላጊ ነገር ነው:: ይሄ ምንም የሚያከራክር ነገር አይደለም:: እኔን ትንሽ የሚያሳስበኝ Interim Poverty Reduction Strategy Paper (IPRSP) ላይ መንግስት በአቀረበው ወረቀት ወይም ጽሑፍ ላይ በለጋሽ ሀገሮች እና በለጋሽ ድርጅቶች መካከል በሚካሄደው ውይይት በመንግስት እና በለጋሽ ድርጅቶች ወይም መንግስታት የሚያደርገው ውይይት እንደዚሁም በእንደዚህ ያሉ መድረኮች ላይ አንድ በጣም በጣም መሰረታዊ የሆነ ነገር ጎሎ አያለሁ:: ይኸውም የስራ መፍጠር ጉዳይ ነው:: እንደተባለውም ምርት ካላደገ እድገት ካልኖረ ምንም ነገር ለመስራት አይቻልም:: ነገር ግን የምርትና የእድገት መኖር በራሱ ድህነትን ይቀንሳል ማለት አይደለም::

በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ በእድሜ ምክንያት፣ በአቅም መድከም ምክንያት ወላጆች በመሞታቸው፣ በብዙ ልዩ ልዩ ምክንያቶች በእድገትና በምርት አለም ውስጥ ለመሳተፍ የማይችሉ ብዙ አሉ:: እዚህ ደግሞ አሁን ቁጥራቸው እየበዛ እና እየበረከተ እየሄደ ነው:: IPRSP ይኼንን ጉዳይ ተመልክቶታል ወይ ወይስ አልተመለከተውም? እኔ እንዳነበብኩት ከሆነ ምንም ስለዚህ ነገር አይናገርም:: ሁለተኛ

በኢትዮጵያ ውስጥ የስራ አጡ ቁጥር እጅግ እየሰፋና እየበረከተ ነው የሄደው፣ ስታትስቲክሱ በዚህ በኩል አከራካሪ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ትንሽ በምናውቀው መሰረት ለመናገር ያክል ወደ 45 በመቶ የከተማ ነዋሪ በተለይ እድሜያቸው ከ16-49 የሚሆነው ስራ የሌለው ነው። ይሄ ግማሽ ማለት ነው። ይኼም በከተማ ማለት ነው የገጠሩን ለጊዜው እንተወው። እንግዲህ የኢኮኖሚው እድገት ለህዝቡ እንዲዳረስ ከተፈለገ ለእነዚህ ስራ አጦች ስራ የመፍጠር ጉዳይ በጣም አሳሳቢና አስፈላጊ ነገር ነው ማለት ነው። ሁለተኛ የህዝቡ ቁጥር አሁን 3% በማደግ ላይ ነው። ይሄም እንግዲህ በበለጠ Labour Force Participation Rateን ከሱ ጋር ስናመጣጥነው ወይም ስናስተያየው ኢትዮጵያ ውስጥ ወደ 800,000 አዲስ ስራ መፍጠር ይኖርብናል። ከህዝቡ ቁጥር እና እድገት ጋር ለመሄድ እንግዲህ 45% ያህል ወይም 30%ም እንበለው በእውነቱ ሰፊ ነው ማለት ነው። በጣም ከፍ ያለ ቁጥር ነው በስራ አጥነት ጎራ ያለው ማለት ነው። በዚያ ተጨማሪ ላይ ደግሞ የህዝቡ ቁጥር መጨመር አለ በአመት 800,000 መጨመር አለብን ማለት ነው። ስራ የመፍጠር ኃላፊነቱ ግዴታው እጅግ በጣም ከፍ ያለ ነው ማለት ነው።

እንግዲህ እድገት በራሱ፣ የስራ ዕድል መፍጠርም በራሱ አይፈጥርም በሌሎች አፍሪካ ሀገሮች ያየነው ነገር ነው። ምንድነው Jobless Growth የሚሉት ነገር ኢኮኖሚያቸው በጣም ጥሩ እና ቶሎ እያደገ ሊሄድ ይችላል ነገር ግን ስራ የመፍጠር አቅም ግን እንደድሮው ሳይሆን እንዲያውም ሊቀንስ ይችላል እና ይኼ ማለት ምንድን ነው? ጉድለቱ የሚገናዘብበትን መንገድ ማሰብ አለብን ማለት ነው። አንድ ብዙ የተነገረ ነገር አለ ለምሳሌ የግል ዘርፍ (Private Sector) እንዲያድግ ነካካ ተደርጓል ደግሞ የስራ ነክን ጉዳይ በተመለከተ የተነገረ ነገር አለ መንግስትም ከፖሊሲ አንፃር ብዙ ኃላፊነት ያለበት ይመስለኛል ያንን መመልከት ይኖርብናል። መንግስት የካፒታል ዋጋን፣ የደመወዝን እንዲሁም የሌሎች ነገሮችንም ጨምሮ ሁሉን ማየት አለበት ማለት ነው። በጥቅሉ (Wage Policy) ማለት ነው። እኔ ከእነዚህ ሁሉ በጣም ችግር መስሎ የሚታየኝ የመንግስት ፕሮግራሞች ምን ያህል ነው ስራ ለመፍጠር የሚችሉት የሚባለውን ጥያቄ ወይም ደግሞ ምን አይነት ፕሮግራም ብናካሂድ ነው ስራ ለመፍጠር የምንችለው የሚለውን ጥያቄ መርምሮ መተግበር ያስፈልጋል። በዚህ ነጥብ ላይ ብዙ መናገር ቢቻልም ለጊዜው በዚሁ ልተወው።

*የአቶ ብርሃነ መዋ መልስ*

በመጀመሪያ የቀረቡት ጥያቄዎች እንደጥያቄ አግባብነት አላቸው ግን መልስ ለመስጠት ብዙ የሚያስቸግሩ አይደሉም። መጀመሪያ ሀብትን ስለማካፈል እና ሀብትን ስለማፍራት ስንመለከት ማየት ያለብን ሀብት ማካፈል ማለት ማኀበራዊ ኃላፊነትን መወጣት ማለት አይደለም። ይኼ በግልፅ ሊቀመጥ ይገባል። ማኀበራዊ ኃላፊነትን መወጣት ሌላ ጉዳይ ነው፤ ሀብት ማካፈል ማለት ደግሞ ሌላ ጉዳይ ነው። ከዚህ አንፃር ስንሄድ ማተኮር የሚኖርብን ሀብትን ማብዛት ላይ መሆን ይኖርበታል። ሀብት በሚበዛበት ጊዜ ማኀበራዊ ኃላፊነትን በአገናዘበበት መልኩ መሆን ይኖርበታል። በቅርብ ጊዜ የአዲስ አበባ Chamber of Commerce አንድ ስትራቴጂክ ፕላን እየሰራ ነበር። በዛ ላይ በግልፅ የተቀመጠ ነገር አለ የሀብት ማብዛት ጉዳይ ማኀበራዊ ኃላፊነትን በአገናዘበ መልኩ መሆን አለበት ቅድም እንደተጠቀሰው ሕብረተሰባችን ውስጥ አቅመ ደካማ የሆኑ ችሎታ ያነሳቸው በእድሜ ያረጁ ወዘተ... ብዙ የህብረተሰብ ሸክም የሆኑ አሉ አሁን እነሱን Care ማድረግ ያስፈልጋል። አዎ ይኼ ማኀበራዊ ኃላፊነትን መወጣት እንጂ ሀብትን ማካፈል አይደለም። ግን አንዱ እየሰራ ሌላው መስራት እየቻለ ግን መስራት ለማይፈልገው ሀብት ማካፈል ሌላ ጥያቄ ነው። ይኼ ማኀበራዊ ኃላፊነትን መወጣት ማለት አይደለም። ይህንን በእንደዚህ አይነት መልኩ ልንገነዘበው ይገባል። አሁን ያለው ካፒታሊዝም በእርግጥ ካፒታሊዝም መልኩን ቀይሮ Natural Capitalism የሚል አዲስ ነገር ነው እየመጣ ያለው። ማለት ምንድነው የአካባቢን ሁኔታ የሕብረተሰብን ሁኔታ ያገናዘበ የሃብት ማካበት ማለት ነው። የማኀበራዊ ግዴታን እየተወጣን ማለት ነው። በዚህ መልኩ እንዲታይልኝ እጠይቃለሁ።

ሁለተኛ በግብርና በኩል ያለውን በሚመለከት እሱም ብዙ የሚያጨቃጭቅ አይመስለኝም። ምክንያቱም ለአለፉት 8 ዓመታት በADLI ነው የሄድነው ነገር ግን At the end of the day ምን ላይ ደርሰናል? ሦስት አራት የሚሆኑ ምሳሌዎችን ልሰጣችሁ እችላለሁ።

- ጅንጅብል ያመረቱ ነጋዴዎች ጅንጅብላቸውን ለመሸጥ ባለመቻላቸው ሁለተኛ ጅንጅብል ወደማምረት አንገባም ብለው አሉ (ምንጭ፤ አዲስ ዘመን ጋዜጣ)
- በምስራቅ ጎጃም የምግብ እህል ያመረቱ ገበሬዎች በዚህ ዓመት ከመንግስት Fertilizer አንቀበልም አሉ። ለምን? ምክንያቱም ምርታችንን የምንሸጥበት ቦታ የለንም።

ያለማዳበሪያ ደግሞ የምንበላውን ያህል ማምረት እንችላለን አሉ።

☝ በደቡብ አካባቢ በከፍተኛ ደረጃ ቡና ያመረቱ ገበሬዎች አሁን የዕርዳታ ማስተባበሪያ ዕርዳታ እየሰጣቸው ነው እየበሉ ያሉት። ምክንያቱም መሸጥ አልቻሉም።

እንግዲህ ሌላ ሌላ ማስረጃ ማምጣት ይቻላል። በተለይ ደግሞ በነጋዴው Store ውስጥ ምግብ ተከማችቶ ታጭቆ ነው ያለው። በመቶ ሺህ የሚቆጠር ኩንታል እህል አለ። ሰው ግን ለመግዛት ስለማይችል እርዳታ ማስተባበሪያ እየረዳው ነው ያለው።

ይኼ ነው እንግዲህ የADLI ውጤት። በዚህ እንቀጥል ካልን አሁንም መቀጠል እንችላለን። ምናልባት ብዙ እህል ማምረት እንችላለን ነገር ግን እየለመንን ማብላት ይኖርብናል። ሀብት ከተፈለገ ግን የService Sector እና የProduction Sector በተጨማሪም የTurism Sector እንዲዳብር equally ለግብርና የተሰጠውን ያህል አንዲያውም ቢቻል በተለይ በምርት በኩል፣ በተለይ በኢንዱስትሪው ከግብርናም የተሻለ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። አንድ ምሳሌ ልስጣችሁ ሁለት ዓይነት የኢኮኖሚ አካሄድ አለ። አንደኛው ሰፕላይ ማርኬት (Supply Market) ነው። ይሄ ማለት አምራቹ የፈለገውን ያመርታል። ምክንያቱም ሁልጊዜ ገበያ ላይ እጥረት ይኖራል ስለሚባል ነው። ሰፕላይ ማርኬት ግን በእዝ ኢኮኖሚ ወይም በሶሻሊዝም ያለ አካሄድ ነው። ስለዚህ ሁልጊዜ እጥረት ስለሚኖር ሰፕላይ ማምረት ብቻ ነው። ኮንሲዩመር ምርጫ ስለሌለው ያንኑ ዕቃ በቀረበለት ዋጋ ይገዛል። ስለዚህ አሁን ደግሞ እዚህ አይነት የገበያ ስርዓት ውስጥ አይደለንም ያለነው። አሁን ኮንሲዩመር ማርኬት (Consumer Market) ላይ ነው ያለነው። ኮንሲዩመር ማርኬትን ስናስብ ማየት ያለብን ማንኛውም ፕሮዳክሽን ዲማንድ ድሪቭን መሆን እንዳለበት ነው። ግብርናም ብንመለከት የግብርና ምርቶችን ብቻ ስናመርት ወይም ደግሞ የእርሻ ምርቶች ሊያድጉ ስለሚችሉ ብቻ አይደለም ማምረት ያለብን። ለእርሻ ምርቶቻችን ገበያ እንደሚኖር ስናረጋግጥ ነው ማምረት ያለብን። This is the rule of the game. ምርጫ የለንም። ለግሎባል ማርኬት ለማቅረብ አቀባባዩ ነጋዴ ያስፈልገናል። የእርሻ ምርታችንን ወደ ሀብት ለመቀየር ኢንዱስትሪ ያስፈልገናል።

ስለዚህ ለኢንዱስትሪ ከፍተኛ ትኩረት ያልሰጠ፣ ለአገልግሎት ሴክተር ከፍተኛ ትኩረት ያልሰጠ፣ ለንግዱ ከፍተኛ ትኩረት ያልሰጠ፣ ገበሬው ላይ ብቻ ያንዣበበ ያውም ለኢንዲቪዡዋል ገበሬ ይሄን በ3% እያደገ ላለ ገበሬ መሬቱ አይሰፋም ነገር ግን ሰው ነው እያሰፋ የሚሄደው። ከሶስትና ከአራት አመት በኋላ አሁን የያዘውን መሬት ሊያገኝ የሚችል ገበሬ እዚያ ላይ አነጣጥሮ ድህነትን እናጠፋለን ማለት የሚያስኬድ መንገድ አይደለም የሚል አመለካከት አለ። ሌላው የግል ክፍል ኢኮኖሚ መዳበርና መንግስት ላይ የማነጣጠሩ ጉዳይ ነው ይሄንን ሙሉ ለሙሉ ለመነጋገር ያስቸግራል። የግል ክፍል ኢኮኖሚው ሰዎች ወይንም ደግሞ በግል ሀብት ላይ ያሉ ሰዎች በእነሱ በኩል ማሟላት የሚገባቸው ነገሮች የሉም ለማለት ያስቸግራል። ብዙ ነገር ግን ዋናው መሰረታዊው ነገር ሊያሰራ የሚችል የስራ ሁኔታ መፍጠር ዋናው ተግባር ሊሆን ይገባል። ከዛም አልፎ ሁኔታዎችን ራሱ በጋራ ለመስራት አሁን ባለንበት ደረጃ የካፒታል ደረጃ የShare Market ለመክፈት የንግዱ ኅብረተሰብ ይከፈትልን እያለ መንግስት ይህን ፖሊሲ ለመደገፍ እንኳን ያልቻለበት ደረጃ ላይ ነው ያለነው። በዚህ ኢንቫይሮሜንት ውስጥ ታዲያ እንዴት አድርጎ ነው ባለሃብቱ የህግ መሰረት በሌለበት መልክ በጋራ ሽርክና ለመስራት የሚችልበት ሁኔታ አለ የምንለው? በጣም አስቸጋሪ ነው። በእርግጥ እንደተባለው በየመድረኩ የግል ባለሀብቱ ራሱን እየፈተሸ ነው መስተካከል ያለበትን ሁሉ እያስተካከለ ነው። ለሚያስተካክላቸው ነገሮች ግን ሕጋዊ የሆነ ድጋፍ ሕጋዊ የሆነ መሰረት በተለይም ደግሞ ተደማጭነት ያስፈልገዋል። አንድ ምሳሌ ለመስጠት ያህል የግል ኢኮኖሚው ከመንግስት ጋር ተባብሮ መስራት አለበት። አዎ ይሄንን ፖሊሲ መንግስትም ይደግፈዋል። ነገር ግን መንግስት ከነማን ጋር ነው እየተነጋገረ ያለው ብለን ብንጠይቅ ጥቂት Hand Picked (የተመረጡ) ከሆኑ ነጋዴዎች ጋር ነው እየተነጋገረ ያለው። እሱም የመሰለውን ሰዎች እየመረጠ ነው ያለው (Not from the organized private sector) መንግስት ይሄን አመለካከት መቀየር አለበት። ምክንያቱም የተደራጀ የግል ሴክተር የራሱ የሆነ Sectoral Interest ብቻ ነው የሚያወራው። ስለ ነጠላ ኢንተርፕራይዝ ችግር አይደለም የሚያወራው። ስለዚህ እነዚህ ነገሮች ከተስተካከሉ እርግጥ እንደተባለው የግል ባለሀብቱ ማስተካከል ያለበትን አስተካክሎ ድህነትን ከዚህች ሀገር ለመቀነስ ብቻ ሳይሆን ለማጥፋት ይችላል የሚል ዕምነት አለኝ። በሌላ በኩል የተሰጠው አብዛኛው አስተያየት ስለሆነ ልንቀበለው ይገባል። ግን መንግስት ሰራተኛን በመቅጠር በኩል ከግል ክፍለ-ኢኮኖሚው ጋር ሲታይ የግል ክፍለ-ኢኮኖሚው ለሚያወጣው ለእያንዳንዷ ብር የበለጠ ሰራተኛ ለመቅጠር ይችላል ከመንግስት በተሻለ የሚል ዕምነት አለ።

## ሁለተኛና ሦስተኛ አቅራቢዎች

በአጠቃላይ የወ/ሮ ሙሉ እና የአቶ ኃ/መስቀል የአስተሳሰብ መስመር አንድ ዓይነት ነው:: የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ በከፍተኛ ኢንዱስትሪ ሆነ በአነስተኛና በጥቃቅን (Informal) ሴክተርንም ጨምሮ በአጠቃላይ የግል ንግድ (የግሉ ዘርፍ) በድህነት ቅነሳ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው ነው ያሰመሩበት:: ነገር ግን ይሄን ለድህነት ቅነሳ የሚጠበቅበትን ሚና እና ተግባር ለመፈፀም የማይቻልበት ሁኔታ ላይ እንዳለ ሁለቱም ተናጋሪዎች በዝርዝር ገልፀዋል:: ይኸውም ተስማሚ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ብሎም የፖሊቲካ ሁኔታ አለመኖሩን ጠቁመዋል:: በተለይ መንግስት ያወጣው እርሻን መሰረት ያደረገ የኢኮኖሚ ፖሊሲ በሀሳቡ ጥሩ ቢሆንም ነገር ግን ድህነት ከመቀነስ አኳያ ያለው አስተዋፅዖ ደካማ እንደሆነና ይሄም ብዙ ነገሮች እንደሚጎድሉት በአቅራቢዎቹ ተጠቁሟል::

በአጠቃላይ በግሉ ሴክተርና በመንግስት በኩል ተባብሮ የመስራት ሁኔታ የላላ መሆኑን ጠቁመው ድህነትን መቀነስ ካስፈለገ የጠበቀ ግንኙነትና አብሮ የመስራት ሁኔታ ብሎም መተማመንን መፍጠር እንዳለብን አስገንዝበዋል::

## የሁለተኛው ዙር ውይይት

1. ሁለቱ ተናጋሪዎች ከንግድ ምክር ቤት የመጡ እንደመሆናቸው የንግድ ምክር ቤት ሚና በቀጥታ ምንድነው? ከሚል ጋር የተያያዘ ነው ጥያቄው::

   ይሄንንም የምጠይቀው ዛሬ ከሰማነው አስደንጋጭ ነገር አንዱ በኢትዮጵያ ውስጥ የእርሻ ምርት ቢያድግና ቢትረፈረፍም እንዲያውም የበለጠ ችግር ውስጥ እንደምንገባ ነው የሰማነው:: አሁን ይሄን አልመለስበትም:: በቂ ማስረጃም ተሰጥቶናል:: ይሄ በሚሆንበት ጊዜ የእኔ ጥያቄ ገበያና ምርትን ማስታረቁ ዋናው ሚና የመንግስት ነው ወይ? የእሱ ከሆነስ ይህን ማድረግ ይችላልን? እኔ አይመ-ስለኝም:: ዛሬም የሰማነው ብዙውን ነገር መንግስት እንደማይችል ነው:: ስለዚህ ነጋዴ ብዙ ነገር ማድረግ እንደሚችል ሰምተናል:: በዚህም አንፃር ቢሆን ሁለቱን ለማስታረቅና አንድ ጋር ለማምጣት ዋናው ሚና የነጋዴው ይመስለኛል:: ለማለት የፈለኩት በኢትዮጵያ ውስጥ የተለመዱት በቆሎና ስንዴ ብቻ ሳይሆን ሌሎች በዓለም ገበያ ተፈላጊነት ያላቸውና ጥሩ ዋጋ የሚያስገኙ ሰብሎች እንዲመረቱ ማድረግ የሚችለው ነጋዴው ነው::

   የኢትዮጵያ ገበሬ የዓለምን ገበያ እየዳሰሰ ወይም ኢንተርኔት ላይ ሰርች እያደረገ ይኼንን ባመርት ይሻላል ሊል አይችልም:: መንግስት ደግሞ በትዕዛዝ ይኼን አምርት ይሄንን አታምርት ቢለው ተገቢ አይደለም:: የሚሰራም ነገር አይደለም:: ነገር ግን የኢትዮጵያ ነጋዴዎች በሌሎች ሀገሮች ለምሳሌ እንደጎረቤታችን እንደ ኬኒያ ባሉ ሀገሮች ነጋዴ የሚጫወተውን ሚና በመጫወት አንዳንድ በጣም ተፈላጊና ጥሩ ዋጋ የሚያስገኙ ሰብሎችን እንዲያመርት ገበሬውን የመምራት ሚና መጫወት አለባቸው:: ለምሳሌ ኬሚካል (ፔስቲሳይድ) የሚተካ ዓይነት ተክል ካለ ያንን በብዛት እንዲያመርትና ተጠቃሚ እንዲሆን ወይም ደግሞ ኦርጋኒክ ሰብሎች የበለጠ ዋጋ ስለሚያወጡ በኢትዮጵያ ሁኔታ ደግሞ እነሱን ማምረት ስለሚቻል ያልተበከሉ ምርቶችን ማምረት ስለሚችል የኢትዮጵያ ገበሬ ያንን በማስተዋወቅና ለዚያ ገበያ በመፈለግ እና እራሳቸው ነጋዴዎች ተጠቅመው ገበሬውንም የገበያ ተጠቃሚ ማድረግ ይችላሉ:: ይህንንም የኢትዮጵያ ነጋዴዎች በግለሰብ ደረጃ ሊያደርጉት የሚችሉ አይመስለኝም:: ነገር ግን ቢያንስ በምክር ቤቶች በኩል ሊያደርጉ ይችላሉ:: እና በዚህ በኩል ምን ዓይነት ጥረት እየተደረገ ነው? ማለትም ምክር ቤቶች እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ምን ዓይነት አዎንታዊ ሚና እየተጫወቱ ነው? ይሄ ነው ጥያቄዬ:: አመሰግናለሁ::

2. እኔ ሁለት ዓይነት ድህነቶች ይታዩኛል:: አንደኛው በግል፣ በዜግነት፣ በተራ ሰውነት የሚታየው ሲሆን ሌላው ሀገራዊ ድህነት ነው:: የእኔ ትኩረት በሀገራዊ ድህነት ላይ ነው:: ሀገራዊ ድህነት ላይ ደግሞ የግል ሴክተር አለ፣ መንግስት አለ:: በድሀ ሀገር ውስጥ ሀብታሙ መንግስት ብቻ ነው:: ለዚህም የድህነት መግለጫንና ቁሳዊ አካል ብቻ ትቼ ሌላውን ጉዳይ ብመለከት ፍርሃት፣ ጭንቀት፣ ስጋት፣ ጥርጣሬ በአጠቃላይ ዋስትና ማጣት የመሳሰሉት የድህነት መግለጫዎች ናቸው:: ከዚህ አንፃር ሳየው የእኛ ሀገርና በአጠቃላይ በሌሎችም የደሀ ሀገሮች እንደሚታየው ሀብታሙ፣ ጉልበተኛው፣ ሁሉን ነገር ማዘዝ፣ ማድረግ፣ መፍጠር የሚችል መንግስት ብቻ ነው:: ስለዚህ የግሉ ዘርፍ በመጀመሪያ በእኔ እይታ ከዚሁ ከድህነት ውስጥ ነው የማስገባው:: ድሃ ነው ማለቴ ነው:: ምክንያቱም አሁን ያልኳቸውን መሰረታዊ መለኪያዎችን ወይም ያስቀመጥኪቸውን

ያሚሳል እና ጭንቀት አለበት፤ ስጋት አለበት፤ ጥርጣሬ አለበት:: በአጠቃላይ ዋስትና የለውም ስለዚህ ደህ ነው:: የግሉ ዘርፍ ከድህነት ወጥቶ ከተጽእኖ ወጥቶ ነፃ የሚሆንበትና ለሀገራችን ዕድገት እኩል ተሳታፊ የሚሆንበትን ስልት መቀየስ አለበት:: የድህነት መቀነስ ስትራቴጂ እዚህ ላይ ትኩረት መስጠት አለበት:: ስለዚህ ባለቤቱ እራሱ የግሉ ዘርፍ ታግሎ በበኩሉ ማድረግ የሚችለውን አስተዋፅዖ ለማሚላት መታገል አለበት:: ማንም ሊሰጠው አይችልም:: ስለዚህ ለመታገል ምን ያህል ዝግጅቱ እንዳለ ምንአልባት ከአቅራቢዎቹ በኩል ያለውን አስተያየት ቢገለፅልን?

3. ሶስቱም ተናጋሪዎች በአቀረቡት ፅሁፍ ውስጥ ጥሩ አድርገው ሁኔታዎችን ዳሰዋል:: ትልቁ ችግር ብለው ያቀረቡት መንግስት ራሱ አመቺ (Enabling) ፖሊሲዎችን አለማውጣቱና አለማሻሻሉ አንዳንድ መወሰድ የሚገባቸውን እርምጃዎች አለመውሰዱ እና ከጊዜ ወደጊዜ ደግሞ ከሕዝቡ ብዛት ጋር ስናየው በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ1981 ላይ የአንድ ሰው ግሬይን ፐር ካፒታ 180 ኪ.ግ. ነበር (ለእያንዳንዳችን የሚደርሰን ማለት ነው):: አስር ዓመት ቆይተን በ1989 እና 1990 ወደ 140 ኪ.ግ. መጣ:: በ1995 97 ኪ.ግ. ላይ ነን:: ልዩነቱ እንደዚህ ነው የሚወርደው:: ይሄ ሩጫ የት ነው የሚያደርሰን? ስለዚህ ይሄ የሚጠቁመን ምንድነው ይሄ ሁሉ ኮምፕሌይን ኤንድ አድቫይስ ከየቦታው የሚመጣው ከኢንተርናሽናልም ከናሽናልም ከሲቪል ሶሳይቲውም ከሁሉም ከሁሉም ሰርቫይቫል (Servival) ስትራቴጂ ውስጥ እንዳንገባ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልገናል ማለት ነው:: ሁላችንም ለማለት ነው:: ፖሊሲ አውጪዎች (Policy Makers) በጣም መጠንቀቅ እንዳለባቸውና ኢኮኖሚክ ፖሊሲ (ADLI) ቅድም እንደተነገረው የሕዝቡ ተሳትፎ ይህንን ፖቨርቲ ሪዳክሽን የሚባል ወረቀት በጥሞና ማየት የሚገባ ነው::

እኔ በአጠቃላይ ለማለት የፈለኩት አሁን ስለፖቨርቲ ሪዳክሽን ወይም ስለድህነት፣ ስለዕድገት የተለያዩ ተያያዥ ጉዳዮች ተነስተዋል:: ብዙውን ጊዜ የእኛ ችግር ምንድነው ክርክር በምናነሳበት ጊዜ ወይም አንድ ነገር ላይ በምንወያይበት ወቅት በተለይ ስለ ዴቨሎፕመንት የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ከእኛ ላቅ ብለው ከሚገኙ ኢንተርናሽናል ድርጅቶች ወይም በበለፀጉ ሀገሮች ፎርዋርድ በሚደረጉ አስተሳሰቦች ላይ ነው:: እነዚህ አስተሳሰቦች ይለወጣሉ በየጊዜው:: በእነዚህ ላይ እየተንደረደርን ብዙ ጊዜ ራሳችንን ለመገምገም ነው የምንሞክረው:: ይህ አንዱ ችግር ይመስለኛል:: እንደ አንድ ሀገር እኛ ምንድነው የምንፈልገው? የሚለውን ነገር በምናይበት ጊዜ ግን በታሪክም ከልምድም መነሳት አለብን:: በመሰረቱ እድገት ያስፈልጋል:: እድገት ሲመጣ ደግሞ የሕዝቡ ኑሮ መሻሻል ቅድም በተባለው በየደረጃው ባሉት መለኪያዎች መሻሻል መታየት አለበት:: ስለዕድገት ስናስብ ከልምድም ከታሪክም የታዩ መሰረታዊ ነገሮች አሉ:: አንድ ሀገር ሊያድግ የሚችለው ወይም እስከ አሁን ድረስ አደጉ የምንላቸው አንፃራዊ በሆነ መልኩ ነው:: ዕድገት ማቆሚያ የለውም አደጉ የምንላቸው ናሽናል ሪሶርስ ያላቸው ወይም ኢንዶውድ የሆኑ ሀገሮች ለምሳሌ የአረብ ሀገሮች ቅድም ከአፍሪካም ቦትስዋና ተነስቷል ቦትስዋናና ሌሎች ሪሶርስ ኖሯቸው የሕዝብ ብዛታቸው ትንሽ ሆኖ በዛ ሀብት በከፍተኛ ደረጃ ገቢ አግኝተው እና ቤኒቮለንት ገቨርንመንት ኖሯቸው የሕዝባቸውን ኑሮ ማሻሻል የቻሉ ናቸው:: የአረብ ሀገሮች ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ናቸው:: የቦትስዋና የተባለውም ይሄው ነው::

ሌላው ክላሲካል በሆነ መልኩ እድገት የታየባቸው ሀገሮች ናቸው እንግዲህ ብዙ ጊዜ እኛ ነፃ ገበያ ነው፣ ካፒታሊዝም ነው፣ ዲሞክራሲ ነው፣ የምንላቸው ነገሮች እንዴት ከራሳችን ጋር ማዋሀድና ማየት አለብን የሚለው ነገርን የምንስት ይመስለኛል:: እኔ በበኩሌ የግል አስተያየቴ ነው ይኼ ደግሞ ብዙ ረዥም ጊዜ የፈጀ ቀደም ሲል በጀመሩት ሀገሮችና በከፍተኛ ደረጃ በደረሱ ሀገሮች የሚታይ የዕድገት ሂደት ነበር:: ያ ዛሬ እነሱ የደረሱበትን ደረጃ መሠረት በማድረግ የተለያዩ ቲዮሬቲካል መነሻዎችን በታዳጊ ሀገሮችም ይኸንን የራሳቸው የሆነውን የዕድገት መነሻ እንዲከተሉ ያስገድዷቸዋል፤ ወደ ኋላ እንዲቀሩ ያደርጋል ያን የሚያደርጉት ግን ከራ ሳቸው ፍላጎት ተነስተው ነው ዛሬ ግሎባላይዜሽን የሚባለው ነገር፣ ዓለም በነፃ ገበያ መተዳደር አለበት የሚባለው ነው:: በእርግጥ /ግሎባላይዜሽን/ ነፃ ገበያ የሚባለው ነገር በምን ኮንቴክስት ነው መውሰድ ያለብን ወይም ማጥናት ያለብን ወይም የራሳችንን ዕድገት እንዴት ነው የምንመራው? የሚለውን ማየት ያለብን የሚለው ነገር ትልቅ ነጥብ መሆን ያለበት ይመስለኛል::

ሌላው ናሽናሊዝም ነው:: ለምሳሌ እንደ ቻይና፣ ኮሪያና ህንድ ያሉ ሀገሮችን በመሰረቱ እነዚህ ሀገሮች ያደጉት ናሽናሊዝም ሊዲንግ ፎርስ በመሆኑ ነው:: በነገራችን ላይ ለዕድገት ፖሊቲካል ፎርስ፣ ፖሊቲካል ጋይዳንስ በጣም አስፈላጊ ይመስለኛል:: በዛሬም ሁኔታ የፖሊቲካ ኮምፕሮማይዝ፣ ናሽናል ኮምፕሮማይዝ፣ ናሽናል ፍሬምወርክ የተለያዩ ኅብረተሰቦችን እንወክላለን

የሚሉ ወገኖች በአንድ ፍሬምወርክ ላይ መስማማት የግድ ይመስለኛል። ዕድገትን ለማምጣት በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የተለያየ አስተሳሰብ የተለያየ አመለካከት ያለን ሰዎች በምን መልኩ ነው ናሽናል ፍሬምወርክ መፍጠር የምንችለው በምን መልኩ ነው ዕድገት ላይ መስማማት የምንችለው? በእርግጥ ላንስማማ እንችላለን ነገር ግን በትንሹ የሚያስማማውን ወይም የሚያቀራርቡን ነገሮች ካሉ በዛ ደረጃ አብረን የመስራት ፍላጎቱና ትልቁም ነገር ትግል መደረግ ያለበት እዚህ ላይ ይመስለኛል ከዛ በኋላ ያለንን አቅም መርምረን ቅደም ተከተል ማውጣት አለብን። መንግስት ለእድገት በጣም ቁርጠኛ በመሆን ለምሳሌ የተወሰኑ ወደኋላ የቀሩ ክልሎች አሉ እነሱን ደረጃ በደረጃ የሚያሳድግበትን ትልም መንደፍ ይኖርበታል። ስለዚህ እኔ ለማለት የፈለኩት በኛ ችግር ላይ ያለንን አመለካከት ልቅም አድርገን መጀመሪያ ለችግሮቹ ያለንን የመፍትሄ አመለካከቶች ማስታረቅ መቻል አለብን። ከዛ ተነስተን ነው በጋራ ለዚህች ሀገር ምን መስራት አለብን የሚለውን ማሰብ ያለብን።

*የወ/ሮ ሙሉ መልስ*

ተራውን ሳልጠብቅ መጀመሪያ ወደ እኔ የተጠየቁትን ጥያቄዎች ልመልስና በእርግጥ ሁሉን ነገር መንግስት አይስራ ስል እኔ የግሎች ብቻ ይስሩ ማለቴ አይደለም። መንግስት ሰሌክቲቭ በሆኑና ሀገርን ሊያሳድጉ በሚችሉ በተለያዩ ነገሮች ውስጥ ሁሉም ጋር ንግዱም ጋር የተለያየ ነገር ውስጥም ባይገባ ለማለት ነው ሌሎች የተለያዩ ስራ ዎች የመንግስት ድርሻዎች የሆኑ ከፍተኛ ትኩረት የሚፈልጉ የአገር ጉዳዮች ላይ ማተኮር አለበት ለማለት ነው። ስለተሰጠኝ ኮሜንት አመሰግናለሁ። ሌላ የገ/መስቀል ጥያቄን መመለስ አይሁንብኝ እንጂ የንግዱ ክፍለ-ኢኮኖሚ ግብርና በሚያመጣው ምርትና በሚያሳድገው የምርት ሁኔታ ላይ ሚና ሳይጫወት ቀርቶ አይደለም። በግልም ይሁን በቼምበርም ደረጃ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይቷል። እኔ እራሴ በግል እንኳን ያደረኩትን ብነግራችሁ፣- አንዳንድ ጊዜ በአንድ አንድ ሀገሮች ችግር ሲፈጠር ለሌላው ሀገር መልካም አጋጣሚ የሚሆንበት ሁኔታ አለ አሁን ለምሳሌ በከብቶች መኖ ችግር ምክንያት ዓለም በተለይ እነዚህ ሀብታም ሀገሮች አውሮፓውያን፣ አሜሪካንም፣ ሌሎች ሀገሮችም መኖ ይፈልጋሉ። መኖ በሚፈልጉበት ጊዜ እኛ ውዳቂ ወይም ምራጭ የምንለው በቆሎም ይሁን ስንዴም ይሁን ማሽላና ጤፍ የሆነ ቅልቅል ብቻ ለከብት ይፈልጉታል። ይኼን እንኳን ቀርቶ በጥሩ ሁኔታ የተመረተውን በቆሎ ኢሊባቡር አካባቢ ወይም ጎጃም አካባቢ በኩንታል እስከ 15.00 ብር አገኘሁ በየወሩ የአንድ መርከብ መጠን ያለው ምርት የሚቀበለኝ ሳፕላየር አገኘሁ። በሚሊዮኖች የሚቆጠር ነው በመርከብ ሙሉ ማለት በየወሩ በጣም ትልቅ መጠን ነው። በኢትዮጵያም በጣም በቂ ምርት አልነበረም ያንን ለማቀበል ነገር ግን ባለው የመሰረተ ልማት (ኢንፍራስትራክቸር) ችግር ያው እንደሚታወቀው ችግራችን ቪሺየስ ሰርክል ነው የሚሆነው። የአንድ ጊዜ ጥረት ሳይሆን የረጅም ጊዜ ጥረትና ችግሮችን ለመፍታት መንግስትም የግሉ ኅብረተሰብም ሁሉም ይንቀሳቀስ የምንለው ለዚህ ነው። በቆሎውን እኔ ጅቡቲ ለማድረስ በኩዊንታል ከጎጃም አዲስ አበባ ድረስ 30.00 ብር ከአዲስ አበባ ጅቡቲ ለማድረስ 40.00 ብር አንድ ላይ 70.00 ብር የትራንስፖርት ዋጋ ብቻ እንግዲህ ይታያችሁ 15.00 ብር የገዛሁት በቆሎ በኩዊንታል 70.00 ብር ጨምሬበት ኢንተርናሽናል ዋጋ ላይ ተወዳዳሪ ሊያደርገኝ አልቻለም። ሌሎች ሀገሮች ከዚህ ባነሰ ማቅረብ ቻሉ። የትራንስፖርት ችግር፣ የመሰረተ ልማት ችግር፣ ሁሉም አንድ ላይ በመሆኑ ችግራችን የሚጠላለፈው ለዚህ ነው።

ይሄንን የተጠላለፈ ችግር ለመፍታት የአንድ ጊዜ አይደለም ረጅም ጊዜ የሚፈጅና ተከታታይ ጥረት የሚፈልግ ነው። ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (አይ.ኤም.ኤፍ.) ብድር ለማግኘት ብለን አንድ ሰሞን ዘፈን እንዘፍናለን ከዛ በኋላ እንተወዋለን። አንድ ሰሞን ሆይ ሆይ እንላለን ከዛ እንተወዋለን። ያ መሆን የለበትም የሚለውን ጉዳይ ለማንሳት ነው። ችግሩ የተጠላለፈና ቪሺየስ በመሆኑ በሴቶች ጉዳይ አንድ ዘፈን ይዘፈናል። ብድር ከተገኘ በኋላ ይቀራል። ድህነትን ለመቅረፍ ሌላው እስክስታ ይመታል ይቆማል እንደዚህ አይነት ስራ አይደለም መሰራት ያለበት። የዛ አይነት ቀጣይ ጥረት ይጠበቃል። ከግሉ ኅብረተሰብ ከመንግስትም ከሲቪል ሶሳይቲውም። ሲቪል ሶሳይቲው የተለያየ ስራ አለው ሌሎች ሀገሮች በጣም በብዙ የሚቆጠር ሲቪል ማኅበረሰብ አሉ። ለምሳሌ አለም አቀፍ ወይም ሀገር በቀል መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (NGOs) አሉ። እዚህ በተለያዩ የፖለቲካ ችግር ይሄ ሌላ አላማ ይኖረዋል በሚል ነፃነት ብዙም የላቸውም። ለመንቀሳቀስና ለመስራት መንግስት ብቻውን ችግሮች ሊቀርፍ አይችልም። የተለያዩ ሀገር በቀል ድርጅቶች ፣ የውጭ ድርጅቶች በተለያዩ ሁኔታዎች መደገፍ አለባቸው። የንግዱ ኅብረተሰብ የራሱን ድርሻ ሊጫወት የሚችለው እንደተባለው ሁኔታዎች ሲያመቹ ነው። ይሄ ካልተመቻቸ እንዴት አድርጎ ሊሰራ ይችላል? የመንግስትን ቅድም አንስተውታል ፈላጭ ቆራጭ የሚለው ነገር የንግዱ ኅብረተሰብ በተለያየ መንገድ ጥረት ቢያደርግም መንገዶች ብዙ ናቸው እውነቴን ነው የምላችሁ በቲቪ በሬዲዮ በምን የምናየው ጥሩ ነው። አንዳንዴ ስንንቀሳቀስ ጥሩ ጎኖችም አሉ እንቅፋት የሆኑ ጎኖችም ስላሉ። ይሄ እንቅፋት ነው ስንል መንግስት የግሉ ኅብረተሰብ እንደጠላት ማየት የለበትም አንድ ላይ እንደ አንድ ሰው

አይቶ ችግሩን ለመፍታት እንደምናቀርብ ፖዘቲቭሊ ማየት ቢቻል በጋራ ችግር ለመፍታት እንችላለን የሚል ሃሳብ ለማቅረብ ነው::

የቻይና ልምድ ተነስቷል:: ቻይና በጣም ብልጥ ሀገር ናት እንጂ ዝም ብላ ሁሉንም አትሞክርም:: አዲስ ነገር ሲመጣ በአንዲት መንደር ወይም ቀበሌ ተሞክሮ ጥሩ ውጤት ሲያሳዩ ወደየቀበሌው እያሳደገች ፖሊሲ ሲወጣ ሀገሩን በሙሉ እንደኛ በአንዴ አታተለቀልቅም:: እውነቴን ነው ናሽናል ኢንተረስታቸውን በጣም ይጠብቃሉ:: የእኛ ግን ቅድም እንደተባለው ለአንድ ብሔራዊ አላማ ጥቅም የመቆም በመንግስትም በሕዝብም ዲተርምንድ የሆነ እውነተኛ ቆራጥነት የተሞላበት ጄንዊን የሆነ ኤፈርት ይጠይቃል:: የዓለም አቀፍ ሁኔታዎችንም ጠንቅቆ አውቆ በዚያ ብሔራዊ ፍላጎታችንን በማይጎዳ መንገድ እየተንዝን ልማት የሚመጣበትን መንገድ በጋራ መሻትና መጓዝ ያስፈልጋል::

*የአቶ ገ/መስቀል መልስ*

ገበያንና ምርትን በማስታረቅ ረገድ ንግድ ምክር ቤቱ ምን ያደርጋል የሚል ጥያቄ ተነስቷል:: ጥሩ ጥያቄ ነው:: የተመረተው ለገበያ መቅረብ አለበት ልክ ነው:: እንግዲህ የፖሊሲና የስትራቴጂው ጠቀሜታ የሚመረተውን የምርት አይነት አቅጣጫ በማስያዝ ረገድ አስተዋፅኦ ይኖረዋል:: መንግስት ይሄንን አምርት አታምርት አይልም:: ግን ለሀገር ይጠቅማል ለወገን ይጠቅማል ለሕዝብ ይጠቅማል የሚለው ካለ በዛ አቅጣጫ ገበሬም ሆነ ነጋዴው እንዲንቀሳቀስ ፖሊሲና ስትራቴጂ ይነድፋሉ:: የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤቶች ዞሮ ዞሮ እንደምታውቁት የነጋዴዎች ቤት፣ የነጋዴዎች ስብስብ ነው:: ነጋዴዎች በአንድ ቦታ በንግድ ምክር ቤታቸው አማካኝነት የሚያደርጉትን ጥረት ለማገዝ የመንግስት ሚናው ተስማሚ ፖሊሲ እና ስትራ ቴጂ መንደፍ ነው:: ይሄንን እንዲያደርግ የነጋዴውን አመለካከት የነጋዴውን ግንዛቤ መንግስት እንዲያውቀው ከተቻለም ጫና በማድረግ የንግዱን ኅብረተሰብ አመለካከት በሚቀይሰው ፖሊሲና ስትራቴጂ ውስጥ እንዲያካትት ጫና መፍጠር ነው:: እንግዲህ ይሄንን በማድረግ ረገድ በተለያዩ መድረኮች ስለኢንቨስትመንት ፖሊሲ ስለ መሬትም ምናልባትም በቴሌቪዥን በልዩ ልዩ መድረኮች ተከታትላችሁ ይሆናል ንግድ ምክር ቤቱ በመሪዎቹ አማካይነት አቋሙንና አስተያየቱን ገልጿል:: አሁንም በተወካዮች ምክር ቤት በኩል አንዳንድ ጥሪዎች ሲደርሱ አስተያየት የሚሰጥበት ሁኔታ ነው ያለው እንግዲህ የነጋዴውን ሚና ቀደም ብዬ ለመጥቀስ ሞክሬያለሁ:: አዳዲስ ምርቶች ለምሳሌ በብዛት ማምረት ካለብን የሀገራ ችን የከተማው ገበያ ጠባብ ከሆነ የግድ ወደ ውጪ መላክ ይኖርብናል:: እንዴት መላክ ይቻላል? ቅድም እንደተነገረውና እንደሰማችሁትም በቆሎም ችግር አለው:: ገበሬውን ይሄን አምርት ማለት አደገኛ ነው::

ምን ይሻላል? እንግዲህ አንዱ መንገድ ኤክስፖርተብል ፕሮዳክት ፈልጎ ከሌሎች ሀገሮች ኤክስፒርያንስ አምጥቶ እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ መቼም እንደመጣ ስራ ላይ አይውልም:: የግድ በምርምር ስርአት አማካኝነት ያስተራረሱን ዘዴ አዲስ ፕሮዳክት አዲስ ምርት አይነት ከሆነ ኤክስፖርተብል ከሆነ የሚስማማውን ቦታ መምረጥ ያስፈልጋል:: እዚህ ላይ ነጋዴው ይህን ለማድረግ ዝግጁና ፈቃደኛ ነው ግን ይህ የረጅም ጊዜ የልማት ጥረት እንደመሆኑ መጠን በዚህ አቅጣጫ ለሚሳተፍ ነጋዴ ልዩ የገንዘብም የፖሊሲም ድጋፍ ሊሰጠው ይገባል:: በተለይ በዚህ አቅጣጫ የሚሳተፍ ነጋዴ የተለየ ድጋፍና ድጎማ ያስ- ፈልጋል:: ምክንያቱም ሊከስርም ይችላል:: መንግስት ብቻውን ሳይሆን በኢንተርናሽናል ደረጃ ኢንተርናሽናል ዶነርስ ድህነትን እንቀርፋለን በሚል ተነሳሽነት ያላቸው ኢንተርናሽናል ኦርጋናይዜሽንስ፣ የዓለም ባንክም ሆነ ሌሎችም በዚህ ለሚሰማራ ነጋዴ የተለየ ድጋፍ የሚሰጡበትን ስርዓት የሚፈጥሩበትን ዘዴ መፍጠር አለባቸው:: እስካሁን ግን እንደዚህ አይነት ነገር የለም::

እስካሁን በዚህ ረገድ ለሚሳተፍ አንደኛ ገበሬው መሀል ገብቶ ይሄንን ራዕዩን ምኞቱን ለማከናወን የሚፈልግ ነጋዴ ተመቻችቶለታል ወይ? ገበሬው መሀል ገብቶ አንድ ለምሳሌ በአውሮፓ ሲዞር አንድ አይነት ምርት ለኢትዮጵያ ይሆናል ብሎ ሀሳብ ይኖረዋል ያንን ወስዶ ቦታ አግኝቶ ገበሬው መሀል በምርምር ስርፀት የሚስማማውን አይነት የአስተራረስ ዘዴ ለማግኘት የተመቻቸለት ሁኔታ ሊኖር ይገባል:: እንግዲህ ነጋዴው እንዲህ አይነት ሁኔታ ከተመቻቸለት ይሳተፋል:: ይሄ አንዱ ችግራችንን በተለይ በግብርናው መስክ መቅረፍ የሚያስችለን አካሄድ ይሆናል::

ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ ዋናው የነጋዴው ሚና ቅድም ለማለት የሞከርኩት ገበሬው ምን ማምረት እንዳለበት ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር የገበያ መረጃ ለገበሬው ማቅረብ በዚህ መሰረትም ምርት እንዲመረት ማመቻቸት ነው:: በእርግጥ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ላይ ኮንትራት ፕሮዳክሽን የሚባል አባባል አለ:: እንግዲህ ነጋዴው ከገበሬ ጋር ተነጋግሮ ይሄንን ምርት አምርት እኔ በዚህ ዋጋ እገዛለሁ የሚልበት ሁኔታ በተጨባጭ ተግባራ ዊ የሚሆንበት ሁኔታ ወይም ስርዓት ሊፈጠርለት እና ድጋፍ ሊሰጠው ይገባል:: ነጋዴው በመሰረቱ

የንግድ ምክር ቤት አባላቱ ስብስብ እንደመሆኑ መጠን በአጠቃላይ ኢነብሊንግ ኢንቫይሮሜንት ከመፍጠር አኳያ ሁኔታዎችን ለሁሉም የንግዱ ኅብረተሰብ በሚያመች መልኩ ፖሊሲዎች እንዲቀየሱ አልፎም ለአባል ነጋዴዎች ልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚሰጧቸው ይኖራሉ፡፡

ሌላው ለሀገራዊ ደህንነት ትኩረት መስጠት ነው፤ ይሄ እርግጥ ነው፡፡ አንድ ነጋዴም ሆነ ሌላ ማንኛውም ዜጋ መፍራት የለበትም ጥርጣሬ ሊኖረው አይገባም ስጋት ሊኖርበት አይገባም፡፡ ባለው ሕግና ስርአት መሰረት ያለምንም ፍርሀትና ስጋት የሚሰማውን ማድረግ የሚገባውን ማድረግ የሚችለውን ሁሉ ለመፈፀም መቻል አለበት፡፡ ነገር ግን አጠቃላይ የፖለቲካ ሂደቱ እራሱ ይሄንን የሚያበረታታ እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ረገድ የንግዱ ኅብረተሰብም በንግድ ምክር ቤቱ አማካኝነት አንደኛ ዲሞክራቲክ መብቱን በሚጠቀምበትና መረጃ የሚያገኝበት በፖሊሲ ረገድ መካተት የሚገባቸውን በንግድ ምክር ቤቱ አማካኝነት መንግስት የሚያውቅበትን ሂደት እያመቻቸ እየተነጋገረ የሚያደርገው ነገር ነው፡፡ እንደተባለው መታገልም ይኖርበታል ማለት ነው፡፡ ይሄ ይሄ እየተካሄደ ነው መቼም አንድ መጨረሻ ላይ የተናገሩት ሰው እንዳሉት አንድ ሀገር ታሪኩን፣ ባሕሉንና እሴቱን መሰረት ማድረግ አለበት፡፡ ለሚያደርገው ነገር ሁሉ ሁልጊዜ አዲስ መሆን አይችልም፡፡ ከዛ ከወጣ፣ ከተነቀለ የሚያደርገው ነገር ሁሉ ውጤታማ ላይሆን ይችላል፡፡ ገበሬው የራሱ ባሕል፣ እሴት፣ ታሪክ፣ አለው፡፡ ስለአካባቢው ከሱ የተሻለ የሚያውቅ የለም፡፡ ምናልባት አንድ ፕሮፌሰር ባለሙያ በየአ-ቅጣጫው የተለየ ዕውቀት ይኖረዋል፡፡ የሁሉም ቅንጅት ግን ውጤታማ ሊሆን የሚችለው እና ምሁራን፣ ሌላ ባለሙያ፣ የእርሻ አዋቂው ወዘተ... ከገበሬው ጋር የሚገናኙበትና አብረው የሚሰሩበት ሁኔታን ማመቻቸት ወሳኝ ይሆናል፡፡

እንደተባለው ግሎባላይዜሽን አለ፡፡ ግሎባላይዜሽን የነፃ ገበያ አካሄድ ነው፡፡ ሌላ አማ ራጭ ካለ ያንን አማራጭ ማየት፣ ከግሎባላይዜሽን ውጭ መንቀሳቀስ አትችልም ከተባለ ደግሞ በግሎባላይዜሽን ማዕቀፍ ውስጥ ጥቅሟን ማክሲማይዝ የምታደርግበት ሁኔታ ማመቻቸት ይጠበቅባታል፡፡ ይሄ ተደርጓል ወይ? አላየሁም፡፡ እንግዲህ ባለው በአለም ስርዓት ውስጥ ነው ያለነው፡፡ በዚህ ውስጥ መኖር እንችላለን? አብረን መሄድ እንችላለን? አንችልም ካልን ደግሞ አማራ ጭ አለን ወይ? ነው ከሌለን በዛው ስርዓት ውስጥ ለምሳሌ በማደግ ላይ ያሉ ሀገሮች በዚህ ግሎባላይዜሽን ሂደት ውስጥ አንዳንድ የተለየ አድቫንቴጅ ይኖራቸው ይሆናል፡፡ ያንን በአግባቡ ማወቅና በዛ መጠቀምና ማድረግ የሚገባንን ነገር ማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ ምርጫው የእኛ ነው፡፡ ስንመርጥ ደግሞ ተለይተን ለብቻችን ማድረግ የምንችለውና የማንችለውን ማወቅ የሚጠቅሙንን መለየት ይኖርብናል፡፡ አመሰግናለሁ፡፡

*የወ/ሮ ሙሉ ተጨማሪ መልስ*

አቶ ገ/መስቀል ባለው ላይ ለመጨመር ግሎባላይዜሽን እኛን ላያፈናፍን ይችላል ብለን መንግስትም በዚህ ሰበብ እጁን አጣምሮ ይቀመጥ ማለታችን አይደለም፡፡ ባለው ዘመን (ኤራ) ድሮ የሰሩት ሊሰሩ ችለዋል፡፡ አሁን ግን እንዴት ሊሰራ ይቻላል? ጥናት መደረግ አለበት፡፡ እንዴት እንሰራለን የሚል ሪወርክ መደረግ አለበት፡፡ መንግስት ሌላ ሲስተም መፍጠር አለበት፡፡ አንዳንድ ነገሮችን እንደገና ማቋቋም ባይችልም፣ ዶሜስቲክ ኢንደስትሪዎችንም ፕሮቴክት ማድረግ ባይችልም መርዳት የሚችልባቸው ብዙ ቀዳዳዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ ኢምፖርት ኢንደስትሪ ሪስትሪክት አድርጋለሁ ቢል አይፈቅድለትም፡፡ ግን መሬት በነፃ እሰጣለሁና የመንግስት ይዞታን አሳድጋለሁ ቢል የሚከለክለው የለም እና የተለያዩ ዘዴዎች ፈጥሮ ከዚህ ችግር የምንላቀቅበትን እና ወይም ኤክስፖርታችንን የምናሳድግበት ወይም ኢምፖርት ሰብስቲትዩት የምናደርግበትን ልዩ

# FSS Publications List

***NOTE:*** All FSS publications (except **MEDREK**) are distributed by Image International, a local book agent. Its address is P.O.Box 80766, Addis Ababa; tel. 251-1 51 09 54; e-mail: image@telecom.net.et

**FSS Newsletter**

*Medrek* (Quarterly since 1998. English and Amharic)

**FSS Discussion Papers**

No. 1. *Water Resource Development in Ethiopia: Issues of Sustainability and Participation.* Dessalegn Rahmato. June 1999

No. 2. *The City of Addis Ababa: Policy Options for the Governance and Management of a City with Multiple Identity*. Meheret Ayenew. December 1999

No. 3. *Listening to the Poor: A Study Based on Selected Rural and Urban Sites in Ethiopia.* Aklilu Kidanu and Dessalegn Rahmato. May 2000

No. 4. *Small-Scale Irrigation and Household Food Security. A Case Study from Central Ethiopia.* Fuad Adem. February 2001

No. 5. *Land Redistribution and Women's Land Rights.* Yigremew Adal. September 2001

No. 6. *Environmental Impact of Development Policies in Peripheral Areas: The Case of Metekel, Northwest Ethiopia.* Woldeselassie Abbute. Forthcoming, 2001

No. 7. *The Environmental Impact of Small-Scale Irrigation: A Case Study*. Fuad Adem. Forthcoming, 2001

**FSS Monograph Series**

No. 1. *Survey of the Private Press in Ethiopia: 1991-1999.* Shimelis Bonsa. 2000

No. 2. *Environmental Change and State Policy in Ethiopia: Lessons from Past Experience.* Dessalegn Rahmato. 2001

**FSS Conference Proceedings**

1. *Issues in Rural Development. Proceedings of the Inaugural Workshop of the Forum of Social Studies, 18 September 1998.* Edited by Zenebework Tadesse. 2000

2. *Development and Public Access to Information in Ethiopia.* Edited by Zenebework Tadesse. 2000

3. *Environment and Development in Ethiopia.* Edited by Zenebework Tadesse. 2001

4. *Food Security and Sustainable Livelihoods in Ethiopia.* Edited by Yared Amare. 2001

5. *Natural Resource Management in Ethiopia.* Edited by Alula Pankhurst. 2001

*(Continued on next page )*

(Continued from previous page )

**Consultation Papers on Poverty (series)**

No. 1. *The Social Dimensions of Poverty.* Papers by Minas Hiruy, Abebe Kebede, and Zenebework Tadesse. Edited by Meheret Ayenew. June 2001

No. 2. *NGOs and Poverty Reduction.* Papers by Fassil W.Mariam, Abowork Haile, Berhanu Geleto, and Jemal Ahmed. Edited by Meheret Ayenew. July 2001

No. 3 *Civil Society Groups and Poverty Reduction.* Papers by Abonesh H. Mariam, Zena Berhanu and Zewdie Shitie. Edited by Meheret Ayenew. August 2001.

No. 4 *Listening to the Poor.* Oral Presentation by Gizachew Haile, Senait Zenawi, Sisay Gessesse and Martha Tadesse. In Amharic. Edited by Meheret Ayenew. October 2001.

**Books**

1. *The View from Below: Democratization and Governance in Ethiopia.* Edited by Bahru Zewde and Siegfried Pausewang. Forthcoming (Co-published by FSS)

**Special Publications**

*Thematic Briefings on Natural Resource Management, Enlarged Edition.* Edited by Alula Pankhurst. Produced jointly by the Forum for Social Studies and the University of Sussex. January 2001

## Forum for Social Studies

The Forum for Social Studies (FSS) is an independent, non-profit institution engaged in policy-oriented research on the development challenges facing Ethiopia. It provides an open forum for the discussion of public policy and promotes public awareness. FSS believes that encouraging broad participation in policy debates is an important contribution to the democratic process. To achieve its goals, FSS organizes public conferences, and publishes and distributes its research findings to policy makers and other government officials, civil society institutions, professionals, the business community, donor agencies and the public at large. This publication is meant to encourage public discussion of the issues concerned and their policy implications.

## Consultation Papers on Poverty

These publications are based on papers presented and discussions held at FSS' Poverty Dialogue Forum and are meant to stimulate debate and reflection on the Government's poverty initiatives.

## Address

Forum for Social Studies
P.O.Box 3089
Addis Ababa, Ethiopia

Tel. (251-1) 55 61 21/12 95 79/55 20 25
E-mail: fss@telecom.net.et

**Financial support for the Policy Dialogue Forum and this publication was provided by the FRIEDRICH EBERT STIFTUNG to which we are grateful.**

**We also wish to thank the Royal Netherlands Embassy for its generous financial assistance to FSS.**

Layout by *Mihret Demissew*